# አማካሪ እና ደጋፊ

## የአሰልጣኝ መምሪያ

ወደ አማካሪ እና ደጋፊነት ዓለም እንኳን በደህና መጣችሁ፡፡ በአራት ክፍሎች በተዘጋጀ በዚህ የስልጠና መርሃ ግብር የአማካሪ እና ደጋፊነት አገልግሎት ምን እደሚመስል እንመለከታለን፡፡ ይህ ስልጠና የተዘጋጀው በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን ለማማከር እና ለመደገፍ ለተዘጋጁ አገልጋዮች ስለሆነ፤ ከዚህ መርሃግብር የሚገኘውን ዕውቀት ለተለያዩ ቤተክርስቲያን አውድ መጠቀም ይቻላል፤ የዚህ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ስልጠና ዓላማ የእናት ቤተክርስቲያን መጋቢያን ቤተክርስቲያን ለመትከል ጥሪ እንዳላቸው የምታምኑባቸውን አገልጋዮች ለማሰልጠን የሚረዳ ነው፡፡ ይህ ሰርቶ ማሳያ ለእግዚአብሔር ክብር የሚያመጡ አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን ለመትከል የሚያስችል አስፈላጊ የሆኑ መርጃዎችን በመስጠት የፈሰሰው ሰው ኃይል፣ ጊዜ፣ ጉልበት እና ሌሎች ግብአቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያግዛል፡፡ ውጤታማ የሆነ የቤተክርስቲያን ተከላ ጤናማ ቤተክርስቲያናትን በማብዛት የእግዚአብሔርን መንግስት ለማስፋት ይረዳል፡፡ ይህ የአሰልጣኝ መምሪያ እያንዳንዱን ርዕስ በመዳሰስ ለአሰልጣኝ እንደ መምሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚህ መምሪያ ውስጥ አሰልጣኑን ሊረዳ የሚችል አሳብ ይህን መምሪያ ካዘጋጁ ጸሐፍት በእያንዳንዱ ርዕስ ስር እንዲካተትተደርጓል፡፡

multiplication network

more churches, stronger churches

Received Feb. 29, 2020

## ማውጫ

ክፍለ ትምህር 1

አማካሪ እና ደጋፊነት ምን ማለት ነው?................ 3

ክፍለትምህርት 2

አዋቂዎችን ማማከርና መደገፍ.........................14

ክፍለ ትምህርት 3

በማመከር እና መደገፍ ውስጥ ያለ ሕብረት........ 24

ክፍለ ትምህርት 4

የማማከር እና መደገፍ አገልግሎትን መጀመር...... 31

የአማካሪና ደጋፊዎች መከታተያ ቅጽ................ 42

የማማከርና ድጋፍ ታሪክ/ድራማ ክፍለትምህርት..... 45

የቤተክርስቲያኝ ተከላ አገልጋዩ ሀለመ................ 47

የጸሐፊያኑ ማስታወሻ.................................. 48

ማስታወሻ፡- እያንዳንዱ ክፍለትምህርት ከ60 እስከ 90 ደቂቃ ውስጥ መስጠት የሚቻል ሲሆን፤ አንድን ትምህርት ለመጨረስ ከ120 ደቂቃ በላይ ሊወስድ አይገባም፡፡

የብዜት መረብ አገልግሎቶች፤ 2014

በተለየ ካልተገለጠ በቀር ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተወሰዱት ከ1954ቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ነው፡፡

*Masterful Mentoring* እና *Why We Must Mentor Church Planters*

አንደኛው መጽሐፍ በድረ-ገጻችን ላይ በነጻ ታገኙታላችሁ www. multiplicationnetwork.org፡፡

ይህ መምሪያ መጽሐፍ ከዋናው የአማካሪ እና ደጋፊ መጽሐፍ ከዋናው መምሪያ ተወስዶ እና ተሻሽሎ የቀረበ ነው፡፡ ተጨማሪ ማብራሪያዎች "ከጸሐፊው የተሰጠ ማስታወሻ" በሚል ርዕስ በማጠቃለያ ክፍሎች ላይ ይገኛል፡፡

# ክፍለ ትምህርት አንድ

# አማካሪና ደጋፊ ምንድን ነው?

ብረት ብረትን ይስለዋል፥ ሰውም ባልንጀራውን ይስላል። ምሳ 27፡17




## ዓላማ

- ስለአማካሪና ደጋፊ አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን ማገናዘብ
- ከአማካሪና ደጋፊ አገልግሎት ጋር የሚዛመዱ ቁልፍ ቃላትን መዘርዘር

## የአማካሪና ደጋፊ አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች

በቃለ እግዚአብሔር የምናገኛቸው ታሪኮች እንደሚያሳዩን የማማከር እና ድጋፍ ሂደት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታጠቁ እና በእርሱ የሚመሩ ሰዎች አማካይነት የሚፈጸም የእግዚአብሔር ዕቅድ መሆኑን ነው፡፡ አንዱ ትውልድ ሌላውን ያገለግላል፡፡ ወላጆች ልጆቻቸው የተቀደሰ ባህል ይኖራቸው ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን ዕውቀት እንዲያዳብሩ ያግዛሉ፡፡ መሪ የሚከተሉትን ሰዎች እግዚአብሔር ስለሚፈልገው መንገድ እና መሪነት ያውቁ ዘንድ ያዝዛል ያስተምራል፡፡ ምንም እንኳን በርካታ ስለማማከር እና ድጋፍ የሚያሳዩ ታሪኮች ቢኖሩም፤ ለዚህ ሞጁል በማማከር እና ድጋፍ በሚያገለግል አገልጋይና ተገልጋይ መካከል ስላለ ግንኙነት የሚያወሱትን ጥቂቶችን መርጠን አቅርበናል፡፡

በግል ንም በቡድን በመሆን በዚህ የቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቡ፡፡ ተሰታፊዎች የምንባብ ክፍሉን ተከፋፍለው እንዲያነብቡ ማድረግ የሚቻል ሲሆን፤ ጥያቄዎችንም ለመመለስ ይረዳል፡፡

BIBLICAL EXAMPLES OF MENTORING

**ሙሴ እንደ ማማከርና ድጋፍ አገልጋይ**

ሙሴና ሎሌው ኢያሱ ተነሡ፤ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወጣ። ዘፀ 24፡13

**በርናባስ እንደ አማካሪና ደጋፊ ከጠርሴሱ ሳኦል/ጳውስ ጋር**

በርናባስ ግን ወስዶ ወደ ሐዋርያት አገባውና ጌታን በመንገድ እንዴት እንዳየውና እንደ ተናገረው በደማስቆም በኢየሱስ ስም ደፍሮ እንዴት እንደ ነገረ ተረከላቸው። ሐዋ 9;27

ማርቆስ ከተባለው ዬሐንስ ጋር

በርናባስም ማርቆስ የተባለውን ዮሐንስን ደግሞ ከእነርሱ ጋር ይወስድ ዘንድ አሰበ፤ ሐዋ 15፡37

## ሙሴ እንደ ማማከርና ድጋፍ አገልጋይ

ዘጸ 17፡9-14፤ 24፡13-18፤ 32፡17-18፤ 33፡11፤ ዘኍ 11፡24-29፤ 14፡6-9፣30፣38፤27፡18-23፤32፡12፤34፡17፤ ዘዳ 1፡38፤3፡21-22 ፣28፤31፡3፣7-8፣14፣23፤32፡44-46፤34፡9፤ኢያ1፡1-18፤24፡31፤መሳ 2፡7-11

በግል ንም በቡድን በመሆን በዚህ የቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቡ፡፡ ተሳታፊዎች የምንባብ ክፍሉን ተከፋፍለው እንዲያነብቡ ማድረግ የሚቻል ሲሆን፤ በመጨረሻ ጥያቄዎችንም ለመመለስ ይረዳል፡፡




እነዚህ ከላይ ያነሳናቸው ባህሪያት በታሪክ አጋጣሚ በተስፋው ምድር ይኖሩ ለነበሩ ማህበረሰቦች ወሳኝ ናቸው፡፡

1. የሙሴ እና የኢያሱ ሕብረት እንዴት እንደጎለበተ አስረዱ፡፡

2. በሙሴ ሕይወት ውስጥ የሚገኝና ለኢያሱ የሚጠቅም ምን አይነት ዕውቀት ነበር?

3. እንዴት ነበር ሙሴ ለኢያሱ ዕውቀቱን ያስተላለፈው?

4. ከሙሴ ጋር የነበረውን ህብረት ተጠቅሞ ኢያሱ እንዴት ባለ መልኩ ራሱን አሳደገ?



5. እዴት ነበር ሙሴ ኢያሱን ያስታጠቀው?

___

___

___

6. የእግዚአብሔር ህዝብ በመጨረሻ የዯረሰበት ውጤት ምን ነበር?

___

___

___

## በርናባስ እንዯ አማካሪና ዯጋፊ

ሐዋ 9፡27-29፤ 11፡25-26፤ 15፡36-41፤ ቆላ 4፡10፤ 1ጴጥ 5፡13፤ ሐዋ 12፡25፤ 13፡4-5፤ 13፡13፤ ፊሌሞ 1፡24።

**ከጠርሴሱ ሳኦሌ/ጳውስ ጋር**

በዯማስቆ መንገዴ ሊይ ጌታን ከተዋወቀ እና ካመነ ከሶስት አመት በኋሊ የጠርሴሱ ሳኦሌ ከጌታ ሐዋርያት ጋር ሇመገናኘት ወዯ ኢየሩሳላም ተጓዘ (ገሊ 1፡18)። ይሁን እንጂ በዚያ የነበሩ አማኞች ቀዴሞ ያሳዴዲቸው የነበረን ሰው ሇመቀበሌ አንገራግረው ነበር፤ አሁን ግን ይህ ሰው የአማኙ ማህበረሰብ ህብረት አካሌ ሆኗሌ። በርናባስም ቢሆን ይህን ሰው ወዯ አማኞች እና ሐዋርያት ህብረት ይቀሊቀሌ ዘንዴ እንዯ አማሳኝ ሆኖ ሇማምጣት መወሰኑ የራሱን ተአማኒነት አዯጋ ውስጥ እንዯመጣሌ ያሇ ከባዴ ውሳኔ ነበር። ከተወሰነ ጊዜ በኋሊ ሐዋርያት በአንጾኪያ ያለ አሕዛብ (ከአይሁዴ ነገዴ ውጪ የሆኑ) አማኞችን እንዱጎበኝ፣ እንዱያበረታታ እና እንዱያጠናክር ወዯ ስፍራው ሌከውታሌ። እዚያ እንዯዯረሰ ያስተዋሇው አንዴ ነገር ይህ የአገሌግልት መስክ የጠርሴሱን ሳኦሌ አገሌግልት በበሇጠ ሇማሳዯግ የተመቸ መሆኑን ነበር፤ ሇዚህም ነው ሳኦሌን ከጠርሴስ ወዯ አንጾኪያ ያመጣው። በዚያም በርናባስ ምክር እና ዴጋፍ ስር የጳውልስ አገሌግልት እየበዛ እና እያበበ ሄዯ። እዚህ ሊይ እንዴ የሚተኮርበት ጉዲይ በርናባስ ያሳየን የማማከር እና ዴጋፍ አገሌግልት ወሳኝ ሂዯትን ነው፤ እርሱም ሳኦሌን (አሁን ጳውልስ ተብል ስሙ ተቀይሯሌ) አንዯ ተተኪ በመቁጠር አዱስ የመሪነት ሚናን እንዱጫወት እዴሌ ሰጥቶታሌ። በመንፈስ ቅደስ ምሪት በእርሱ ማማከር እና ስሌጠናስር ያሇውን ወንዴም ጳውልስን ሇተጠራበት ጥሪ ብቁ እንዯ ሆነ አምኖ አሰማርቶታሌ።

- በርናባስ የሚለው ስም በሐዋርያት የወጣለት ሲሆን ትርጓሜውም "የመጽናናት ልጅ ማለት ነው" (ሐዋ 4፡36)።
- የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎቱ በበርናባስ አነሳሽነት የተጀመረ ነው (ሐዋ 9፡27)።
- የእግዚአብሔርን መንግስት ለማስፋት የሚሆን አቅም በሳኦል ውስጥ ተመልክቷል፤ ተገንዝቧልም (ሐዋ 9፡27-29)።
- ለሳኦል የሚሆን የአገልግሎት ስፍራ አግኝቶለታል ደግሞም ከእርሱ ጋር በጋራ አገልግሏል (ሐዋ 11፡25-26)።
- ሳኦል በአገልግሎቱ የተጠቀመበት፤ ምሳሌ የሚሆን የአገልግሎት ሂደትም አሳይቶታል (1ቆሮ 11፡1፤ 2ጢሞ 2፡2)።
- ጳውሎስ የመሪነቱን ስፍራ ይወስድ ዘንድ ለመፍቀድም ችሏል (ሐዋ 13፡7-46)።
- በርናባስ የአዲስ ኪዳንን አንድ ሶስተኛውን ከጻፈው ከጳውሎስ ጎን ለጎን ማርቆስንም በምክር እና ድጋፍ ሲያገለግለው ነበር።

1. የበርናባስ እና ሳኦል/ጳውሎስ ህብረት እንዴት እንደጎለበተ ግለጽ።

በግል ንም በቡድን በመሆን በዚህ የቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቡ። ተሰታፊዎች የምንባብ ክፍሉን ተከፋፍለው እንዲያነብቡ ማድረግ የሚቻል ሲሆን፤ በመጨረሻ ጥያቄዎችንም ለመመለስ ይረዳል።

2. በበርናባስ ውስጥ ያለ ለጳውሎስ የሚያስፈልግ ዕውቀትና ልምድ ምን ነበር?

3. እንዴት ነበር ይህ ዕውቀት እና ልምድ ወደ ጳውሎስ የተላለፈው?

4. ከበርናባስ ጋር የነበረው ህብረት ጳውሎስ በምን አይነት ሁኔታ እንዲያድግ ረዳው?

5. እንዴት ነበር በርናባስ ጳውሎስን ያስታጠቀው?

6. በርናባስ የጳውሎስ አማካሪና ደጋፊ በመሆኑ ምን አይነት አዎንታዊ ውጤት አስመዘገበ?

## ጳውሎስ ከተባለው ዮሐንስ ጋር

1. ለምንድን ነው ጳውሎስ ማርቆስ ከተባው ዮሐንስ ጋር ለመስራት ፈቃደኛ ያልሆነው?

2. በርናባስ እና ጳውስ ምን ነበር የወሰኑት?



በግል ንም በቡድን በመሆን በዚህ የቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቡ:: ተሰታፊዎች የምንባብ ክፍሉን ተከፋፍለው እንዲያነብቡ ማድረግ የሚቻል ሲሆን፤ በመጨረሻ ጥያቄዎችንም ለመመለስ ይረዳል::

3. በርናባስ እና ጳውሎስ አማካሪና ደጋፊ ሲሆኑአቸው የመረጡት እነማንን ነበር?

4. የጳውሎስ እና የበርናባስ አማካሪነትና ደጋፊነት አገልግሎት ውጤት ምን ነበር?




## ጳውሎስ እንደአማካሪና ደጋፊ

ጳውሎስ ከበርናባስ የተቀበለውን የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት በተጓዛቸው የተለያዩ ጉዞዎቹ ሁሉ ተጠቅሞባቸዋል፡፡ በሐዋርያት ስራ መጽሐፍ እና በጳውሎስ መልዕክቶች ውስጥ አስራ ስድስት ሰዎች ከጳውሎስ ጋር እንደሰሩ ተዘግቦልናል፡፡ የሐዋርያት ስራ ጸሐፊው ሉቃስ በጳውሎስ የተለያዩ ጉዞ አብረው የነበሩ ሰባት ሰዎችን ጠቅሶልናል፡፡ ይህም ማለት እነዚህ ሰዎች እነዚህ ሁሉ ሰዎች ከእርሱ ትምህርት እና ከእርሱ ጋር ከነበራቸው ህብረት ተጠቅመዋል እንደማለት ነው፡፡ ምን ያህል ይወድዳቸው እንደነበር ለማረጋገጥ ከእርሱ የተላከላቸውን ደብዳቤ ማንበብ በቂ ነው፡፡ በኤፌሶን ያሉ ቤተክርስቲያን እና በእስያ የሚገኙ ሰባቱ አብያተክርስቲያናት መሪዎች የጳውሎስ የማማከር እና ድጋፍ ውጤቶች ናቸው(ሐዋ19፡10፤ ራዕ 2-3)፡፡ በስተመጨረሻ ጳውሎስ መልዕክቱን በእርሱ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ስር ለነበሩ ሁለት አገልጋዮች ማለትም ለጢሞቴዎስ እና ቲቶ ልኳል፡፡ ጳውሎስ እነዚህን ሁለት አገልጋዮች "በክርስቶስ የወለድኳቸው ልጆቼ" በማለት ይጠራቸዋል፤ ይህ ማለቱ በእርሱ አማካይነት ወደጌታ እንደመጡ የሚጠቁም ንግግር ሊሆን ይችላል፡፡ ጳውሎስ በቀጥታ የእርሱ የማማከር እና ድጋፍ ተገልጋይ ለሆኑት ጢሞቴዎስ እና ቲቶ በሐዋርያት ስራ እና በመልዕክቶቹ ውስጥ የተጻፈውን በመመርመር ለተገልጋዮቹ የጳውሎስ ግልጥ የሆነው ትኩረት ምን እንደነበር ማረጋገጥ ይቻላል፡፡



ሐዋ 16፡1-5፤ 17፡14፤ 19፡22፤ 20፡4፤ 1 ቆሮ 4፡17፤ 2 ቆሮ 1፡1፣19፤ 7፡5-16; 8፡6, 16-24፤ 12፡18; ገላ 2፡1-3፤ ፊሊ 2፡19-22፤ 2 ተሰ 3፡1-3፣ 6፤ 1 ጢሞ 1፡2፣ 18-20፤ 2 ጢሞ 4፡10፤+

1. ጳውሎስ ከወጣት አገልጋዮች የነበረውን ህብረት እንዴት መሪዎችን ለማፍራት እንደተጠቀመበት ግለጽ፡፡

2. ጳውሎስ እንዴት ጢሞቴዎስ እና ቲቶ ሲያውቁት የሚገባውን ዕውቀት እና ልምድ በምን አይነት መንገድ ተረዳ ወይንም እንዴት አወቀ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

3. ምን አይነት እውቀት እና ልምድ ነው ከጳውሎስ ወደጢሞቴዎስ እና ቲቶ የተሸጋገረው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

4. ጢሞቴዎስ እና ቲቶ ከጳውሎስ ጋር የነበራቸው ህብረት እንዴት ባለ መልኩ እድገትና መጎልበት ጠቀማቸው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

5. በምን አይነት ሁኔታ ነበር ጳውሎስ እርሱ የሚያማክራቸውንና የሚደግፋቸውን ያስታጠቃቸው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________



በግል ንም በቡድን በመሆን በዚህ የቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቡ:: ተሰታፊዎች የምንባብ ክፍሉን ተከፋፍለው እንዲያነብቡ ማድረግ የሚቻል ሲሆን፤ በመጨረሻ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይረዳል::




## "አማካሪና ደጋፊነትን" መተርጎም




ለምንድን ነው ሆን ብለን ወይንም አስበንበት ማድረግ ያስፈለገው

> አማካሪና ደጋፊ ማለት "አንድ ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን መንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ ሃብት በማካፈል ሌላን ሰው ለማስታጠቅ የሚወስንበት፤ በጠንካራ ህብረት ውስጥ የሚዳብር ልምድ ነው"
> *–Stanley and Clinton*

ከመጀመሪያው ትርጉም ጋር ተመሳሳይ የሆነ ፍቺ/ትርጉም:-

"ለማንኛውም ዝንባሌ እና ዓላማ፤...ማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ሌሎች በክህሎት፣ ባህርይ እና ለማንኛውም የሕይወት አቀጣጫ በሚያስፈልግ ዕውቀት እንዲያድጉ መርዳት ነው:: ማማከር እና ድጋፍ ሊከናወን የሚችለው በሁለት ሰዎች መካከል ሲሆን ከእነዚህ አንድ ከሌላው የበለጠ ልምድ፣ ዕውቀት እና በእርሱ የምክር እና ድጋፍ አገልግሎት ስር ለሚሰለጥነው፤ ያነሰ ልምድ እና ዕውቀት ላለው ግለሰብ የሚያስተላልፈው አንዳች ነገር ያለው ነው:: ይህ ልምድ እና ዕውቀት ለሰልጣኙ የሚደርስበት መንገድ ማማከር እና ድጋፍ ብለን የምንጠራው አገልግሎት ነው::"

–Osterhouse and Teja




1. አማካሪና ደጋፊነት የ <u>ህብረት</u> ሂደት ነው::
2. በዘፈቀደ የሚደረግ እና አላማ ቢስ ሳይሆን <u>ሆን ተብሎ</u> የሚተገበር ነው፡
3. ደጋፊና አማካሪው <u>የሚያካፍለው</u> ልምድ አለው::

4. ሊተሳሰፉ የሚገባው ነገር (ግብአት እና መረጃ ነው።)

5. ደጋፊና አማካሪው ______ እድገትን ያሳልጣል ______

6. ደጋፊና አማካሪው ______ ያስታጥቃል ______

የዚህን ትርጓሜ ይዘት ግልጥ ለማድረግ ምናልባት ከዚህ በታች የቀረቡትን ተጨማሪ ጥያቄዎች ትጠይቅ ይሆናል፡-

- "የህብረት ሂደት" ምን ማለት ነው?
- የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ግቡ ምንድን ነው?
- የትኞቹ የሕይወት እና የልምድ ከባቢዎች በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ጥቅም ላይ ይውላሉ?
- "እድገት ወይንም ማጎልበትን ማሳለጥ" የዚህ አንቀጽ ትርጉም ምንድን ነው?



1. ደጋፊና አማካሪ ኖሮህ የሚያውቅ ከሆነ ሂደቱ ምን እንደሚመስል ልምድህን አካፍል

2. አማካሪህ ማን እንደነበር ካስታወስክ ስለእርሱ/እርሷ ተናገር

3. በዘፈቀደ የተደረገ ነው ወይንስ የታቀደ?

**"የማማከር እና ድጋፍ" አገልጋይን መተርጎም**




*የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ በኦዲሴይ ቲያትር ውስጥ ኦዲሰስ፤ ቴሌማቹስ የተባለው ልጅ ላይ የተሾመውን ገጸባህርይ ይመስላል። የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ለዚህ ልጅ እንደ አማካሪ እና አስተማሪ ነው።*




ማማከር እና ድጋፍ (*Mentor*) የሚለው ቃል የተገኘው ከአስገራሚው የሆሜር ግጥም ውስጥ ነው። ኦዲሴይ በትሮጆን ውጊያ ለመሳተፍ በዘመተበት ወቅት ልጁ ቴሌማቹስን አስተዋይ እና ታማኝ ለሆነው አገልጋዩ፣ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ (*Mentor*) አደራ ሰጥቶት ነበር የሄደው። የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ለታዳጊዎች ስለማህበረሰብ ልማት፣ ትምህርት እና ስሕይወት የሚያደርጉትን ዝግጅት በብቃት ይወጡ ዘንድ ይመራል። በመሆኑም የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ እንደ ታማኝ

አማካሪ እና አስተማሪ ተብሎ ቢተረጎም ሁሉን ያስማማል፡፡ ተቀባይነት ያለው መዝገበ ቃላት ለአማካሪ እና ደጋፊ የሰጠው ትርጓሜ ካነሳነው አሳብ ጋር ይስማማል፡- "የታመነ አማካሪ እና መሪ"፡፡ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ልምድ ያለው ግለሰብ ሲሆን ከእርሱ ያነሰ ልምድ ያለው ግለሰብን ችሎታ፣ ክህሎት፣ አመለካከት እና አገልግሎትን በተመለከተ ደግሞ ብስለቱን ከፍ ማድረግን ዓላማው አድርጎ በፈቃዱ ህብረትን የሚጀምር ነው፡፡

## "በምክርና ድጋፍ አገልግሎት ስር ያለን ተማሪ" መተርጎም

በአንድ አዋቂ ሰው ምሪት ስር እየሰለጠነ ያለ ወጣት ወይንም በአንድ ድርጅት ውስጥ የሙያ ስልጠና በመውሰድ ላይ የሚገኝን ግለሰብ በምክር እና ድጋፍ ስር ያለን ተማሪ ለመተርጎም ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ እነዚህ ትርጓሜዎች የጥገኝነት እና ቁጥጥር ወይንም በምክር እና ድጋፍ አገልጋዩ የሚሰጥ ጥበቃ ምንነት ትርጓሜን የሚገልጡ ሲሆኑ እነዚህን ግን ከቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ጋር አያይዘን ለመረዳት የተመቹ አይደሉም፡፡

1. በሌሎች ምክርና ድጋፍ ስር የሚሆን ግለሰብ <u>ንቁ</u> ተማሪ ሲሆን እያንዳንዱን የስልጠና ሂደት ከልቡ ይከታተላል፡፡

2. በምክርና ድጋፍ ስር ያለ ተማሪ እያንዳንዱን የሚተላለፍለትን ዕውቀት፣ ክህሎት፣ እይታ፣ ምዘና፣ ወይንም ጥበብ ለ<u>መገምገም</u>፣ <u>ከራስ ጋር ለማዋሃድ</u> እና <u>ለጥቅም</u> ያውለዋል፡፡




ለምንድን ነው በምክርና ድጋፍ ስር ያለ ተማሪ ግለሰብ ከአማካሪና ደጋፊው የሚቀበለውን ዕውቀት መመዘን ወይንም ሙሉ ለሙሉ ካለበት ሁኔታ ጋር ማዋሃድ የሚጠበቅበት?

______________________________________________________

______________________________________________________

## ደቀመዝሙር አድራጊ፣ አማካሪና ደጋፊ፣ አሰልጣኝ

| | | |
|---|---|---|
| ደቀመዝሙር የምናደርገው | አዲስ <u>አማኞች</u> | መሰረት |
| መሰረት መጣል ምክርና ድጋፍ የምንሰጠው | እየተነሱ ላሉ <u>መሪዎች</u> | ቀርጽ ማበጀት |
| የምናሰለጥነው | የመሪነትን ቀርጽ እና ደዘት ማሰናዳት በአገልግሎት <u>የሚሳተፉ ባለሙያዎችን</u> | ማሳለጥ |

## ፍሬ እንዲያፈራ መርዳት

በዚህ ነጥብ ላይ አንድን ጉዳይ በሚገባ ግልጥ መሆን ያለበት አንዳንዶቹ የአማካሪ እና ደጋፊ የጽንሰ ሐሳብ ትንተና ላይ ግራ መጋባትን ይፈጥራሉ። ጌታችን ኢየሱስ በመጨረሻዎቹ የምድር ቆይታው ተከታዮቹ ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ አሕዛብን ሁሉ ደቀመዛሙርት እንዲያደርጉ አዝዞአቸው ነበር። ደቀመዝሙር ማድረግ እና አማካሪ እና ደጋፊነት አንድ አይነት ትርጉም እና ሊደርሱበት የሚገባ የጋራ ግብ አላቸው? ደቀመዝሙር ማድረግን አንዳንድ ጸሐፊያን እንደ እድሜዘመን ስልጠና ሲመለከቱት ሌሎች ደግሞ የክርስትና ሕይወት የመጀመሪያ ስልጠና አድርገው ይወስዱል። አንዳንዶች የአማካሪ እና ደጋፊ አገልግሎትን ደረጃው ከፍ ያለ የደቀመዝሙር ትምህርት አድርገው ይወስዱታል። በምን አይነት መንገድ ደቀመዝሙር ማድረግ ለአማካሪ እና ደጋፊነት አገልግሎት መንገድ ይከፍታል? በምን አይነት ሁኔታስ አማካሪ እና ደጋፊነት ከደቀመዝሙር ከማድረግ እና ከማሰልጠን ጋር ይለያያል?

**ማጠቃለያ**

እናንተን በግል የሚያስደስታችሁ የማማከርና ድጋፍ ይዘቶች ምን ምን ናቸው?

________________________________

________________________________

________________________________

የትኞቹስ የማማከርና ድጋፍ አይነቶች ተግዳሮት ሆኑባችሁ ?

________________________________

________________________________

________________________________

ማማከርና ድጋፍን በራሳችሁ መንገድ ግለጹ ብትባሉ እንዴት ትገልጹታላችሁ?

________________________________

________________________________

________________________________

በድጋፍና ክትትል ስር ያለ ተማሪ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግለጹ ብትባሉ መልሳችሁ ምን ይሆናል?

________________________________

________________________________

________________________________

# ክፍለትምህርት ሁለት

# አዋቂዎችን ማማከርና መደገፍ

*"ሰው በራሱ ውስጥ ያለውን ፈልጎ ያገኝ ዘንድ ታግዘው ይሆናል እንጂ፣ ምንም ነገር ልታስተምረው አትችልም።" -Galileo Galilei*

### ዓላማ

- በመደበኛ የማስተማር ሳይንስ (Pedagogy) እና በአዋቂዎች ትምህርት (Andragogy) መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት
- የቤተክርስቲያን ተካላ አገልጋዩን እንደ አዋቂ ተማሪ ማቅረብ
- የአዋቂዎች የመማር ዘዴቤን ማሰስ
- አዋቂ ተማሪዎች የሚገጥማቸውን ተግዳሮቶች ለይቶ ማወቅ
- ማማከርና ድጋፍ ለአማካሪና ደጋፊውም ሆነ በማማከርና ድጋፍ ስር ለሚገኘው ተማሪ የሚሰጠውን ጥቅም መዘርዘር




### አዋቂዎችን በማስተማር እና ልጆችን በማስተማር መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ

ፔዳጎጂ በአብዛኛው የሚታወቀው እንደ ማስተማር ስልት እና አቀድ ነው። ይሁን እንጂ በቅርብ በአዋቂዎች ትምህርት ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የአዋቂዎች የሚማሩበት ስልት ልጆች እና ወጣቶች ከሚማሩበት ስልት በእጅጉ የተለየ መሆኑን ነው። በዚህ ጥናት መሰረት አዋቂዎች ሲማሩበት የሚገባ አንድራጎጂ የተሰኘ የማስተማሪያ ስልትን ወደማወቅ መራን።




| በመደበኛ የማስተማር ሳይንስ (Pedagogy) | ኣዋቂዎች ትምህርት (Andragogy) |
|---|---|
| ገሪክ παιδος "ፔድዮስ" ልጅ ማለት ሲሆን γωγος "ጎጎስ" ደግሞ ለመምራት የሚል ትርጉም ይኖረዋል | ግሪክ ἀνήρ ሰው ማለት ሲሆን ἀγωγή ማለት ደግሞ መርዳት ወይንም መምራት የሚል ትርጉም ይኖረዋል። |
| ሀ ልጆችን የማስተማር ጥበብ እና ሳይንስ ነው | ይህ አዋቂዎች እንዲማሩ የሚረዳ ጥበብና ሳይንስ ነው |

**ማስታወሻ:-** ብዙ ስልጠና ተሳታፊዎች አንድራጎጂን "አዋቂዎችን ማስተማር" ብለው ትርጓሜ ቢሰጡትም እውነተኛ ትርጓሜው ግን አዋቂዎች የማስተማር ጥበብ እና ሳይንስ ነው። ይህ ልዩነት በጣም አስፈላጊ መሆን ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ ልናስታውሰው የሚገባ ጉዳይ ነው።

## የአዋቂ ተማሪዎች ባህሪያት






በእኛ ምክርና ድጋፍ ስር ለናደርጋቸው ያሉ አዋቂ ተማሪዎች እንደመሆናቸው፤ የራሳቸው የሆነ የእድሜ ዘመን ልምድ እንዳሚኖራቸው አያጠራጥርም በዚህም እያንዳንዱን አዳዲስ መረጃ ለመመዘን እና ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ይጠቀሙበታል፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኞቹ የቤተክርስቲያን ተከላ እና የመጋቢነት አገልግሎት ልምድ ይጎድላቸዋል፡፡ ይህን ምክንያት በማድረግ በእኛ ምክርና ድጋፍ ስር ለመሆን የመረጡ አዋቂ ተማሪዎች አዲስ ወደሆነው የአገልግሎት ስለጠና ለመግባባት ስለወሰኑ፤ ይህን ፍላጎታቸውን ለማርካት እና ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ጥበብ የሞላበት ምክር ይሻሉ፡፡ ታዲያ የአዋቂ ተማሪዎች አማካሪና ደጋፊ በመሆን ማገልገል የሚፈልጉ ግለሰቦች አዋቂዎች በምናይነት መንገድ በተሻለ ሊማሩ እንደሚችሉ አውቀው ይህን ህብረት ከተማሪዎቻቸው ጋር ቢጀምሩ መልካም ነው፡፡

1. <u>በራሳቸው የሚመሩ</u> ናቸው፡፡

2. <u>ውሳኔዎችን</u> ይወስናሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ፡፡

3. በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ <u>ያላቸውን ልምድ</u> ያመጣሉ፡

4. <u>ትኩረታቸው</u> ሊያስወግዱት በሚፈልጉት ተግዳሮት ላይ ነው፡፡

5. <u>ራሳቸውን የሚያነቃቁ</u> እና ለመማር የተዘጋጁ ናቸው፡፡

6. <u>የተማሩትን ወዲያው መተግበር</u> ይፈልጋሉ፡፡

## ለምን የአዋቂ ተማሪዎችን ባህሪያት ማወቅ አስፈለገ?

ለተሳታፊዎችህ ግልጥ ማድረግ የሚገባህ፤ በዚህ ትምህርት ደጋፊ እና አማካሪነት የሚተነተነው የአዋቂ/ጎልማሳ ተማሪዎችን ባህርያት፣ አስፈልጎቶች እና አቅም መሰረት አድርጎ መሆኑን ነው፡፡ ይህን ስትል ደግሞ ሌላ ተያያዥ ጥያቄ ያስነሳል፤ ማማከር እና ድጋፍ ከባህላዊው እና ከተለመደው የትምህርት እና ስልጠና ስልት በምን ይለያል?

1. **አዋቂ ተማሪዎች ራሳቸውን የሚመሩ ስለሆነ፤** አማካሪና ደጋፊ አገልጋዩ የራሱን አጀንዳ በአዋቂ ተማሪዎች ላይ ከመጫን ይልቅ የተማሪዎችን አጀንዳ ትኩረት ሰጥቶ ለመረዳት መሞከር ይገባዋል፡፡ አማካሪና ደጋፊው የራሱን አጀንዳ በተማሪዎቹ ላይ ቢጭን ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?

2. **የራሳቸውን ውሳኔ መወሰን ይችላሉ፤** አማካሪና ደጋፊ አገልጋዩ ተገቢ ውሳኔ ይወስኑ ዘንድ መንገዶችን ያመቻቻል እንጂ የራሱን መልስ አዘጋጅቶ አያቀርብላቸውም። ውሳኔዎችን ሁሉ ራሱ አማካሪና ደጋፊ አገልጋዩ ቢወስን ምን ሊፈጠር ይችላል? የማንስ ውሳኔ ነው?

3. **ያካበቱት ልምድ አላቸው፤** የማማከርና ድጋፍ አገልግሎቱን ሙሉ ለማዳበር የተማሪዎቹን ልምድ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። የተጠራቀመው የአዋቂ ተማሪዎች ልምድ አዳዲስ ዕውቀቶችን እና ልምዶችን ለመመዘን እና ከራሳቸው ጋር ለማዋሃድ የሚረዳ ብቃት ይሰጣቸዋል። እንዴት ነው ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ውጪ ባለ የሙያ መስክ የተካበተ ልምድ እንዴት በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ የሚገጥምን ችግር ለመፍታት ጠቃሚ ይሆናል?

4. **ትኩረታቸው በተግዳሮቶቻቸው ላይ ነው፤** የምክርና ድጋፍ አገልጋዩ የአገልግሎቱን መሰረት ማድረግ ያለበት ምክርና ድጋፍ የሚያደርግላቸው ተማሪዎች ችግራቸውን የሚፈቱበት አማራጭ መንገድ በማሳየት ላይ ሊሆን ይገባዋል። በዚህም ሊተገበር የሚችል መፍትሄ እንዲያመጣ እንጂ አሳባዊ የሆነና የማይተገበር ምክር እንዲሰጥ አይደለም። በምክርና ድጋፍ አገልግሎት ስር ያለ ተማሪ ልምድ እንዴት

በቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ላይ በሚገጥም ተጨባጭ ችግር የመፍትሄ መንገድ ሊሆን የሚችለው?

5. **የራስ ተነሳሽነት ያላቸው ናቸው፤** የምክርና ድጋፍ አገልጋዩ አዋቂ ተማሪዎች እንዲማሩ ማስገደድ አይገባውም፡፡ የራስተነሳሽነት አቅም የሚመነጨው ራሳቸው ያስቀመጡት ግብ ከፍጻሜ ለማድረስ ከውስጥ የሆነ ፍላጎት ሲያድርባቸው ነው፡፡ የአንድን ነገር ዋጋ መቼ ነው የሚማሩት? መቼና ከየት የሚመነጭ ይመስላችኋል፤ ከራስ ተነሳሽነት ወይስ በአስተማሪው አነቃቂ መልእክት?

________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________




6. **በፍጥነት ወደተግባር መለማራት ይፈልጋሉ፤** ከልጆች በተለየ አዋቂዎች የተማሩትን በፍጥነት ወደተግባር መለወጥ ይፈልጋሉ፤ ይህ ካልሆነ ግን ትምህርቱ ዋጋቢስ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ የሚማሩትን በሕይወታቸው ለመተግበር የሚችሉበት መንገድ ካላገኙ ትምህርቱን መከታተል ያቆማሉ፡፡

________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________

## የመማር ዘይቤ

በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ የሚወክለው የተለያየ ብቃት እና ፍላጎት ያላቸው የተለያዩ ቡድኖችን ነው፡፡ የመማር ዘይቤ የሚለውን ቃል የምንጠቀምበት ምክንያት ሰዎች አዲስ መረጃን የሚያሰላስሉበት የራሳቸው የሆነ መንገድ ስላላቸው ነው፡፡

ሁሉም ሰው በአንድ አይነት መንገድ አይማርም ሁሉም ሰው እንዴት መማር እንደሚችል የሚወስን ከማንነቱ ጋር የተሰራ ስልት አለው፡፡ የመማር ልምድ የሚዳብረው አዳዲስ መረጃዎችን ለሰዎች በሚመጥን እና የግለሰቦችን የመማር ዘይቤ ባማከለ ሁኔታ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ተማሪዎች የተማሩትን አዲስ መረጃ እንዲረዱት እና የራሳቸው እንዲያደርጉ መደላደል ይፈጥራል፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡት የመማር ዜቤዎች ብዙ አጥኚዎች የሚስማሙባቸው እና ዕውቅና

የሰጧቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ዝርዝር የመማር ዜቤዎች በማማከር እና ድጋፍ የሚገለገለው ግለሰብ የራሱን የመማር ዘዴቤ እንዲለይ እና የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎቱ የተሳለጠ እንዲሆን የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ያግዘዋል፡፡

1. **የድምጽ/መስማት** ፡- የድምጽ ወይንም የቃል ተማሪዎች እንዲሁ በንግግር የሚሰጥን መረጃ በመቀበል ልዕቀትን ማምጣት ይችላሉ፡፡ እንዲህ ባለው የመማር ዘዴቤ ተፈጥሮአቸው የሆነ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቃል የሚሰጥን ትምህርትና ውይይትን ማስታወስ እና ያንን ዕውቀት ለዘለቄታው ማኖር ይችላሉ፡፡

2. **ተመልካች/የእይታ** ፡- ሲሰጥ የታሰበው መረጃ ሲነበብ ወይንም በስዕላዊ መልክ ሲታይ ከምንም በላይ ያንን መረጃ የማወቅ እና የማስታወስ አቅማቸው ይጨምራል፡፡ ለማስታወስ ስዕላዊ መግለጫዎችን፣ ግራፎችን እና ሰንጠረዥ የሚጠቀሙ ማስረጃዎችን ማዕከል አድርገው ይጠቀማሉ፡፡

3. **የተግባር** ፡- የተግባር ተማሪዎች (ነገሮችን በመነካካት የሚማሩ) ወይንም ከቁስ ጋር መስተጋብር ያላቸው ተማሪዎች ልንላቸው እንችላለን፡፡ እነዚህ ተማሪዎችን ግኙት ፈላጊ ሲሆኑ የመማር አቅማቸው ከፍ የሚለው ነገሮችን በመንካት እና በመመራመር ነው፡፡

4. **ከባቢያዊ** ፡- የመማሪያ አካባቢ ምቹ መሆን፣ በቂ ብርሃን መኖር እና ተገቢ የሆነ የሙቀት መጠን ያለበት ቦታ መማር ከባቢያዊ ተማሪዎችን የመማር አቅማቸው ከፍ እንዲል ማድረግ ብቻ ሳይሆን የተቀበሉትን መረጃ ከማንነታቸው ጋር ለማዋሃድ ብሉም ትምህርቱን ለዘለቄታው ለማኖር ይረዳል፡፡

ከእነዚህ ውስጥ የሚመችህ/ሽ የመማር ዘዴቤ የቱ ነው? ይህ ዘዴቤ እንዴት ለመማር እንደመረጥከው አስረዳ፡፡

በእናንተ የምክርና ድጋፍ አገልግሎት ስር ያለን ሰው እንዴት የመማር ዘዴቤውን እንዲለይ ልትረዳው ትችላለህ?

በእናንተ ምክርና ድጋፍ ስር ያለን ተማሪ የመማር ዘይቤን ማዕከል በማድረግ እንዴት አድርጋችሁ የእናንተን የምክርና ድጋፍ ዘይቤ ተስተካከላላችሁ?



## የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ የሚጋፈጣቸው ተግዳሮቶች

በማማከር እናድጋፍ ስር ያሉ አገልጋዮች አንድ አይነት ጥሪ ይኑራቸው እንጂ የተለያየ የመማር ዘይቤ ያላቸው ከተለያዩ ቡድኖች የተገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ አገልጋዮች ከተለያየ የማህበረሰብ ክፍል፣ የምጣኔ ሃብት ደረጃ እና ሙያ የመጡ ናቸው፡፡ እንደየ ቀለም አቀባበል ብቃታቸው እና ዕውቀት ለዕቀታቸው ልዩነት እንዳላቸው ሁሉ የትምህርት ደረጃቸውም ይለያያል፡፡ በልምዳቸውም ብንመለከታቸው ከጀማሪ መሪ እስከ ልምድ ያከበተ መሪ ድረስ ልናገኝ እንችላለን፡፡ በእኩል ደረጃ ችሎታ፣ ክህሎት፣ ብቃት ወይንም የጸጋ ስጦታ ያላቸው ወይንም የሚጋሩ ሁለት ሰዎች ማግኘት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ትኩረት ቢሰጥበት ትክክል የሚሆነው በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለው አገልጋይ የመጣበት ማህበረሰብም ይሁን የትምህርት ደረጃ ምንም ይሁን ጌታው ለጠራው ጥሪ ብቁ ሆኖ ይገኝ ዘንድ ወደስልጠናው ከገቡበት ጊዜ አንስቶ በሚመቻቸው የመማር ዘይቤ በመጠቀም ማሰልጠን ነው፡፡ አንድ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ወደዚህ ለአገልግሎት ወሳኝ ወደ ሆነ የተግባር ስልጠና ሲገባ አዳዲስ ተግዳሮቶች እንደሚኖሩ እሙን ነው፡፡ በማማከር እና ድጋፍ ስር የመገኘው አገልጋይ ምናልባት የቤተሰቡ መጋቢ፣ አገልጋይ እና ተማሪ ሊሆን ይችላል፡፡

ተሳታፊዎች እንደምሳሌ ሊያነሱት የሚችል፤ እጅግ ከተጎዳ የማህበረሰብ ክፍል የተገኘ እና ክርስቶስን ያመነ፤ በመጋቢዎች እና በሌሎች አማኝ ወገኖች የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ሂደት በሕይወቱ ለውጥ መጥቶ ብቁና በሳል መሪ የሆነ ግለሰብ ካለ እንዲናገሩ እድል ስጥ፡፡

- አንድን በማማከር እና ድጋፍ ስር የሚገኝ ሰልጣኝ፤ በቤተክርስቲያን ተከላ ሂደት ውስጥ ሊገጥሙት የሚችሉትን ተግዳሮቶች እንዲ ገልጡ ተሰታፊዎችን ጠይቅ፡፡

ምናልባት እነዚህ ካሉበት ሌሎች የየዕለቱ ኃላፊነቶች እና ግዴታዎች ተጨማሪ ሊሆኑ ይችላሉ።

1.ያሉበትን ኃላፊነቶች በ ሚዛናዊነት ማስተናገድ።

- ቤተሰብ
- ስራ
- ትምህርት፣ አገልግሎቱን የሚመለከት ስልጠና
- መንፈሳዊ እድገት እና ጤና
- ሌሎች ማህበራዊ ኃላፊነቶች
- ጊዜን በአግባቡ መጠቀም

2. ገንዘብን ማስተዳደር።

- ለቤት ፍጆታ
- ለትምህርት
- ለአገልግሎት
- ስራ (የግል ስራ እየሰራ የሚያገለግሉ ከሆነ)

3. በራስ መተማመንን መጨመር።

- በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጪ በሚሰጡ የሙከራ ስራዎች (የቤት ስራዎች) የሚገጥሙ ትምህርት ነክ ተግዳሮቶች።
- የውድቀት ፍርሃት
- አገልግሎት ነክ ብቃት

4. የድጋፍ ስልትን ማዳበር።

- የቤተሰቡ ስሜት እንዳይጎዳ በአጠገብ ሊቆሙ የሚችሉ ጓደኞች እና ቤተሰብ
- የጸሎት ጓዶች እና የምልጃ ጸሎት
- በማማከርና ድጋፍ ላይ የሚሰራ አገልጋይ

## ከማማከርና ድጋፍ አገልግሎት ሂደት የሚገኝ ጥቅምና ሽልማት

በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኘው ተማሪ:-

- ሸክሙን የሚጋራው አንድ ሰው ይኖረዋል
- ስኬታማ ስመሆን የተሻለ ዕድል አለው
- የሚከታተለው/ተጠያቂ የሚሆንለት ሰው ይኖረዋል

**አገልገዩ የሚጋፈጣቸው ተግዳሮቶች**

1. .ያሉበትን ኃላፊነቶች በሚዛናዊነት ማስተናገድ።

2. ገንዘብን ማስተዳደር።

3. በራስ መተማመንን መጨመር።

ተሳታፊዎችን በቡድን በመመደብ በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለው ሰልጣኝ ሊገጥሙት ይችላሉ ተብለው ከተጠቀሱት ተግዳሮቶች ውስጥ አንዱን በማንሳት ሊፈታው የሚችልበትን አሳብ እንዲያቀርቡ ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ ተግዳሮት አቅርብ።

- በአዲሱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ፈጣን እና ከፍ ያለ ለውጥ ያያል
- ልምድ ካላቸው ሰዎች ጋር ህብረት የማድረግ ዕድል ስለሚያገኝ በሳል ይሆናል
- በሚያስፈልገው ጊዜ ሁሉ በጥበብ የተሞላ ምክር ማግኘት ይችላል
- በወደፊት አገልግሎቱ ሞዴል አድርጎ የሚጠቀምበትን ጤናማ መንፈሳዊ ህብረት ያዳብራል
- ሌሎችን በምክር እና ድጋፍ ለማገልገል ተገቢ የሆነ ሞዴል ይኖረዋል



## የምክር እና ድጋፍ አገልጋዩ:-

## ለምክር እና ድጋፍ አገልጋዩ:-

- ልምድን እና ራዕይን በማካፈል የሚገኘውን ደስታ ያጣጥማል
- የእግዚአብሔርን መንግስት በማጠናከሩ ረገድ የራሱን እገዛ ያደርጋል
- በምክር እና ድጋፍ አገልግሎት በሚፈጠር ህብረት የበለጸገ ይሆናል
- የአገልግቱን መስፋፋት እና ውጤታማነት በሚፈጥረው ተጽዕኖ ይመለከታል
- በአንድ ስፍራ ቀሞ መቅረትን እና የጊዜ ብክነትን ያስወግዳል
- የማይረሳ ስም ይኖረዋል
- ይማራል፤ የሚያስተምሩ በበለጠ ይማራሉና
- የእግዚአብሔርን መንግስት በመገንባቱ ረገድ የበኩሉን አስተዋፅዐ ያበረክታል

ተሳታፊዎችን በሁለት ቡድን በመመደብ፤ አንዱ ቡድን በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ሂደት ሰልጣኙ የሚያገኘውኝ ጥቅም፤ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ የማማከረ እና ድጋፍ አገልጋዩ የሚያገኘውን ጥቅም እንዲዘረዝሩ አድርግ፡፡ ሁለቱም ቡድኖች ያስቀመጡትን ዝርዝር ከታች ከምታገኛቸው ዝርዝሮች (እንዲሁም በተሳታፊዎች መምሪያ ካለው ጋር) አነጻጽር፡፡

## ማጠቃለያ



በማማከርና ድጋፍ ስር ስለሚገኝ ተማሪ ባህሪያት ማወቅ እንዴት የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይን በበለጠ ለመርዳት የሚያስችል ዕውቀት ሊሰጣችሁ ይችላል?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ከተሳታፊዎች መካከል አንድ ሰው ተሰታፊዎች ከዚህ ስልጠና በኂላ በእነርሱ ማማር እና ድጋፍ ስር ለሚሰለጥነው አገልጋይ ስለሚኖረው አስፈልጎት እንዲጸልይ ጠይቅ፡፡ ሌላ ፈቃደኛ ተሳታፊ ደግሞ በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ ለሚሰማራ አገልጋይ በማማከር እና ድጋፍ ሕይወቱን ሊቆርስለት ለተዘጋጀው አገልጋይ እንዲጸልይ ጠይቅ፡፡

**ይህ ክፍለ ትምህርት ለማማከርና ድጋፍ የምትጠቀምበትን አቀራረብ በምን መልኩ ቀይሮታል? በምክርና ድጋፍ ስር ያሉተማሪዎችን ባህሪያት ማጥናትህ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮችን ለማሰልጠን በምን አይነት መንገድ መጠቀም እንዳለብህ ግንዛቤ ሰጥቶሃል?**

# ክፍለትምህርት ሶስት

# በማማከርና ድጋፍ የሚፈጠር ህብረት

*"በመጨረሻጉዞው የተጓዡ እንጂ የመሪው አይደለም" – Daloz*




## ዓላማ

- መልካም በሆነ የማማከርና ድጋፍ አገልጋይና መርዛማ በሆነ የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ ላይ መስፈርትን መዘርዘር
- በምክርና ድጋፍ ስር ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል መልካም የሆኑትን መጥፎ ከሆኑት በመስፈርት መለየት
- በማማከርና ድጋፍ አገልግሎት ውስጥ የሚከሰቱ አደገኛ ሁኔታዎችን መለየት
- የመተማመንን እና የሚስጠር ጠባቂነትን አስፈላጊነት መግለጽ

## የመልካም አማካሪ እና ደጋፊ መገለጫዎች

1. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ ጥሩ አድማጭ ነው::

እንዲህ የሚል የስፓኒሽኛ ምሳሌ አለ "ሁለት ጆሮ እና አንድ አፍ ኖሮን የተፈጠርነው የምንናገረውን እጥፍ እንድንሰማ ነው:: ስለሆነም የምንናገረውን እጥፍ መስማት ይገባናል::" ጥሩ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ብዙ ከማውራት ብዙ መስማትን ይመርጣሉ:: የሚናገሩትም በእነርሱ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ስር ያለውን ሰልጣኝ ጥያቄ ለመጠየቅ እና ለመስማት ነው::

2. መልካም አማካሪ በሕይወት ውስጥ በሚፈጠር " የአሁን ጊዜ" ላይ በትኩረት ይወያያል::

በማማከር እና ድጋፍ አማካይነት የሚፈጠር ህብረት ሰልጣኙ እየተጋፈጠ ያለውን የሕይወት ውጣ ውረድ ማዕከል ያደረገ ነው:: እንደ ትምህርት ምቹ ጊዜ ከተመለከትነው "የአሁን ጊዜ ትምህርት" ለማስተማር የሚረዳ ገጠመኝ በሰልጣኙ ሕይወት በተፈጠረ ጊዜ ማስተማር መልካም ነው ምክንያቱም "ለማስተማር የሚመች ገጠመኝ" ሰልጣኙ ያለበትን ሁኔታ የማይመለከት ወቅት ውስጥ ከማስተማር የበለጠ ውጤታማ ስለሆነ::

ተሳታፊዎች በያሉበት ቡድን፤ በአገልግሎት ዘመናቸው እነርሱም በማማከር እና ድጋፍ ያገለገላቸው ሰው ካለ እንዲናገሩ እድል ስጥ። ይህ ሰው መልካም የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ነበር? ከሆነ፤ ምን አይነት መስፈርት ነው አንድን ሰው መልካም የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ የሚያስብለው? እንዴትስ ይገለጣል?

**የመልካም አማካሪ መገለጫዎች**

1. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ <u>ጥሩ አድማጭ</u> ነው፡፡
2. መልካም አማካሪ በሕይወት ውስጥ በሚፈጠር "<u>የአሁን ጊዜ</u>" ላይ በትኩረት ይወያያል፡፡
3. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋዮች እንደ <u>አዋላጆች</u> ናቸው፡፡
4. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ በእርሱ ምክርና ድጋፍ ስር ያሉ ተማሪዎች <u>አማራጮችን</u> እንዲያዩ ይረዳቸዋል፡፡
5. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ <u>የሚያነሳሳ</u> ነው፡፡
6. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ <u>ጥልቅ አሳቢ</u>ነው፡፡
7. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ



ተሰታታፊዎች በእነዚህ መገለጫዎች ዙሪያ አሳባቸውን እንዲሰጡ 5 ደቂቃ ስጥ፡፡ ከዚያም ሁለት ወይም ሶስት ሰው በአንድ ቡድን በመሆን ከ10 እንሰከ 15 ደቂቃ በመውሰድ መልካም የማማከር እናድጋፍ አገልጋይ ለመሆን ከላይ ከተጠቀሱት መገለጨዎች የትኞቹ እንደሚታዩባቸው እና የትኞቹን በሕይወታቸው እንዲታዩ እንደሚፈልጉ እንዲናገሩ ዕድል ስጥ፡፡



3. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋዮች እንደ <u>አዋላጆች</u> ናቸው፡፡

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች "ሌሎች አዳዲስ አሳቦችን፣ አዳዲስ ክህሎቶችን፣ አዳዲስ ምሳሌዎችን እና የመሆን እና የማድረግ መንገዶችን እንዲወልዱ ያግዛሉ፡፡ አሰልጣኞች ተማሪዎቻቸው ራሳቸውን አሳብ፣ ራዕይ እና ግብ በሚያምጡበት ወቅት በማዋለድ ይረዷቸዋል፡፡" -Vogel

4. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ በእርሱ ምክርና ድጋፍ ስር ያሉ ተማሪዎች <u>አማራጮችን</u> እንዲያዩ ይረዳቸዋል፡፡

ሰዎች አንድ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲገቡ አንድ መፍትሄ፣ አንድ ውጤት እና አንድ ተግባር ብቻ በማየት በአንድ ሰፋራ "ቆመው ሲቀሩ" ይችላሉ፡፡ ታዲያ በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለው አገልጋይ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ሌሎች አማራጮችን እንዲመለከት ይረዳዋል፡፡

5. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ <u>የሚያነሳሳ</u> ነው፡፡

ሁላችንም የሚያምነብን አንድ ሰው እንፈልጋለን፡፡ በተለይ በአገልግሎታችን ያልተሳካልን ሲመስለን እና መደበት ውስጥ ስንገባ፤ ሲያበረታታን የሚችል ባርናባስ ያስፈልገናል፡፡

6. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ <u>ጥልቅ አሳቢ</u> ነው፡፡

ነገሮች ነጭ እና ጥቁር ሆነው ስለማይገኙ እንደ አማካሪ እና ደጋፊ በጥልቀትና በዝርዝር ማሰብ እንዲችሉ ሰልጣኞቻችንን ማበረታታት ይኖርብናል፡፡ እንደ አማካሪ እና ደጋፊ ሰልጣኞችህ ሳሉበት ሁኔታ መፍትሄ በመስጠት እየገጠማቸው ካለው ችግር በላይ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ይገባል፡፡

7. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ <u>ይመራል</u> ፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት የትኞቹ በበለጠ ይገልጹሃል? የትኞቹንስ ይበልጥ ማሻሻል እንዳለብህ ታስባለህ? በምክር እና ድጋፍ የምታገለግሉትን ግለሰብ ለመርዳት ሁኔታውን በሚገባ መተንተን አስፈላጊ ነው፤ ከዚህ በታች ይህን ለማድረግ የሚረዱን አሳቦች ቀርበውልናል፡-

- ከመነሻ ሃተታው ጀምሮ ጠቃሚ የምትሉአቸውን መረጃዎች ግለጹ፡
- ስለሁኔታው የሚሰማችሁን በራሳችሁ መንገድ አሳባችሁን ግለጹ፡፡
- በምክርና ድጋፍ ስር ስለሚሆን ተማሪ የተሰጠውን መሳምት ግለጹ፡፡
- ሌሎች አማራጭ አይታዎችን ከግምት ውስጥ አስገቡ፡፡
- የሚያገለግሉበት አካባቢ ያለው ባህልና እንድምታ በአገልጋዮቹ ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ አስገባ፡፡

## መርዛማ የሆነ የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ መገለጫዎች

መማር ማስተማርን ሊገነባ የሚችል የምክርና ድጋፍ አገልግሎት ውስጥ የሚገኝ ህብረት አለ፡፡ ጥቂት ጊዜ ወስደህ ከዚህ በታች ያሉትን ተመልከት፡፡




1.ያለምንም ዋጋ **ምክር** ይሰጣል፡፡

2. **ያሒሳል/ሂስ ይሰጣል**

3. በምክርና ድጋፍ ስር ያለውን ተማሪ ሁሌም ከየትኛውም ጉዳት **ያስመልጣል**

4. በምክርና ድጋፍ ስር ያለን ተማሪ ተገቢ ባልሆነ መልኩ **ይደግፋል**

5. **የልዩነት አጥር** ይገነባል፡፡

6. በምክርና ድጋፍ ስር ያለን ተማሪውንም ሆነ አሳቡን **ዝቅ አድርጎ** ይመለከታል፡፡

ከላይ ካነሳናቸው ባህሪያት የትኛው የበለጠ በአደገኝነቱ ይታወቃል ደግሞም በእናንተ ሕይወት ተገልጧል ለምን? እንዴት ይህን ባህሪ ከአሳባችን ማፍረስ እንችላለን?

## በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኝ መልካም ተማሪ መገለጫዎች

በመከርና ድጋፍ ስር የሚገኝ
መልካም ተማሪ መገለጫዎች




1. በምክርና ግዳፍ ስር የሚገኝ መልካም ተማሪ ስለሚኖረው ትምህርት ኃላፊነትን ራሱ ይወስዳል፡
2. በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኝ መልካም ተማሪ ንቁ አድማጭ ነው::
3. በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኝ መልካም ተማሪ በንቃት የሚሳተፍ ተማሪነው::
4. በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኝ መልካም ተማሪ የእድሜ ዘመን ተማሪ ነው::
5. በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኝ መልካም ተማሪ ግልጽ ነው::

1. በምክርና ግዳፍ ስር የሚገኝ መልካም ተማሪ ስለሚኖረው ትምህርት ኃላፊነትን ራሱ ይወስዳል::

መልካም የማማከር እና ድጋፍ ተገልጋዮች የራሳቸውን አስፈልጎት እና ምኞት ራሳቸው ይወስናሉ:: ይህም ብቻ ሳሆን ከማማከር እና ድጋፍ አገልጋያቸው ጋር በመሆን መቼ መገናኝ እንዳለባቸው፣ እንዴት ህብረት ማድረግ እንዳለባቸው እና ለምንያህል ጊዜ ለብለባቸው መቆየት እንዳለበት ይወስናሉ::

2. በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኝ መልካም ተማሪ ንቁ አድማጭ ነው::

ልክ እንደማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ሁሉ ሰልጣኙም"አረጋጋጭ አድማጭ ሲሆን ይገባዋል::" በምክርና ድጋፍ አገልግሎት ስር ያለ ሰልጣኝ መሪው የሚለውን መስማት እና በዚያው መሰረት አኗኗሩን መቃኘት ይጠበቅበታል::

3. በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኝ መልካም ተማሪ በንቃት የሚሳተፍ ተማሪ ነው::

- ጠቃሚ ሐሳቦችን ይፈልጋል በተሰጠውም ጊዜ ለዚያ ሐሳብ ያለውን አክብሮት ይገልጣል::
- ለእድገቱ የሚጠቀመውን ማንኛውንም አስፈላጊ ግብአት ከመጠየቅ ወደኋላ አይልም::
- ግልጽ ያለሆነለትን ለማወቅ መጠየቅን አይፈራም::
- በማማከርና ገጋፍ ወቅት በሚፈጠር ህብረት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ነው:
- ምክርና ድጋፍ ከሚያደርግለት ሰው ለምድና የሙያ ዕውቀት መጠቀም የሚገባው ሁሉ ለመጠቀም አያቅማማም::

4. በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኝ መልካም ተማሪ የእድሜ ዘመን ተማሪ ነው::

በምክር እና ድጋፍ የሚያገለግሉ አገልጋዮች በእነርሱ ስር የሚሰለጥኑን ሰው የገጠመውን ችግር መፍታት ወደሚያስችለው ምንጭ (መጽሐፍት፣ ድረገጽ፣ ሌሎች ሰዎች..) ሲመሩው የእድሜ ዘመን ተማሪ እንዲሆን እያደረገው ነው። በማማከር እና ድጋፍ ስር የሚሆኑ ተማሪዎች ራሳቸውን በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ስር ለአጭር ጊዜም ሆነ ለረጅም ጊዜ ማኖር የለባቸውም።

ተሰታፊዎች የመጥፎ ሰልጣኝ መገለጫዎችን እንዲዘረዝሩ ጠይቅ። ከዚያም እንዲህ ያለውን ባህርይ በእነርሱ ማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰው ሲያንጸባርቅ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አሳባቸውን እንዲናገሩ እድል ስጥ።

5. በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኝ መልካም ተማሪ ___ግልጽ___ ነው።

መልካም ሰልጣኞች ግልጽ እና ሃቀኛ ሆነው የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩን ይቀርባሉ። ወሳኝ የሚሉትን መረጃ በፍጹም ለብቻቸው አይዙም፤ ከአቅማቸው በላይ ስለሆነ ጉዳይ እና አስፈልጎት ጥርት ባለ ሁኔታ ማቅረብ ይችላሉ። የዚያን ጊዜ ነው የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ትክክለኛ ምርመራ እና ህክምና ሊያደርግለት የሚችለው።

> **በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኝ ደካማ ተማሪ መገለጫዎች**
>
> 1. ምክርና ድጋፍ በሚሰጧቸው ሰዎች ላይ ለማንኛውም ጥያቄ መልስ ___ጥገኛ___ ናቸው፡
> 2. መታወቅ የሚገባቸውን አዳዲስ አሳቦችን ለመስየትና ለመጠቀም ___ተነሳሽነት___ የላቸውም።
> 3. በምክርና ድጋፍ የሚያገለግሏቸው ሰዎች የሚሰጧቸውን ሐሳብ ___ያቃልላሉ___
> 4. አሁን ያሉበትን ሁኔታ ___ሊተነትኑ___ የማይችሉ ሲሆን፤ አሁንን ችል ብለው ለመጪ ዘመን ያቅዳሉ።

## በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኝ ደካማ ተማሪ መገለጫዎች

1. ምክርና ድጋፍ በሚሰጧቸው ሰዎች ላይ ለማንኛውም ጥያቄ መልስ ___ጥገኛ___ ናቸው፡

2. መታወቅ የሚገባቸውን አዳዲስ አሳቦችን ለመስየትና ለመጠቀም ___ተነሳሽነት___ የላቸውም።

3. በምክርና ድጋፍ የሚያገለግሏቸው ሰዎች የሚሰጧቸውን ሐሳብ ___ያቃልላሉ___ ።

4. አሁን ያሉበትን ሁኔታ ___ሊተነትኑ___ የማይችሉ ሲሆን፤ አሁንን ችል ብለው ለመጪ ዘመን ያቅዳሉ።

## ስለማማከርና ድጋፍ አገልግሎት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

1. ___ዋጋ መስጠት___:- ሌሎችን ዋጋቢስ አታድርግ። (ገላ 5:13፤ ኤፌ 5:21፤ ሮሜ 12:10)

2. ___ሞዴል___:- ጣልቃ አትግባ።

3. ___አበረታታ___:- ተነሳሽነትህን አትጣ። (1ተሰ 5:11፤ ሮሜ 4:13፣ 15:7፤ ኤፌ 4:32)

4. ___ትሁት ሁን___:- ስርአት አልባ አትሁን። (ፊሊ 2:3)




5. አድምጥ :- ለመናገር አትቸኩል::

6. ግልጥ አድርግ :- ነገሮችን እንዲህ ቢሆኑስ ብለህ አትገምት፡

7. በቂ ጊዜ ስጥ:- አቋራጭ መንገዶችን አትጠቀም::

8. ከልስ :- እነዚህን በሚገባ ከማደራጀት ወደኋላ አትበል፡

9. ግብአት ስጥ:- ሁሉንም ነገር ዝግጁ ለማድረግ አትድከም::

10. የአመለካከት አማራጭ አዘጋጅ:- ለአሁን የሚሆኑ ቀለል ያሉ መልሶችን አትስጥ::




ገላ 5:13፤ ኤፌ 5:21፤ ሮሜ 12:10፤ 1 ጢሞ. 5:11፤ ሮሜ 4:13፤ 15:7; ኤፌ 4:32፤ እና ፊል 2:3 እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከእነዚህ ነጥቦች ጋር እንዴት እንደሚያያዙ ተወያዩ::

## የተአማኒነት እና ምስጢር ጠባቂነት አስፈላጊነት






- ማማከርና ድጋፍ አገልግሎት የሚመሰረተው በመተማመንና በሚስጥር ጠባቂነት ነው::
- ያለመተማመን ሚስጥር ጠባቂነት አይኖርም:: ያለሚስጥር ጠባቂነት ደግሞ ሁሉም ተአማኒነት ዋጋቢስ ይሆናል::
- በማማከርና ድጋፍ አገልግሎት ከተማሪዎች ጋር የሚፈጠር ማንኛውም ህብረት ውጤታማ የሚሆነው ወይንም የሚፈርሰው በመተማመን የተነገረ ነገር በተአማኒነት ሲጠበቅ አሊያም ሳይጠበቅ ሲቀር ነው፤ በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኘው ተማሪ ሚስጥሩ የማይጠበቅ ከመሰለው ነገሩ ያበቃለታል::
- ምንም እንኳን በምክርና ድጋፍ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ራሳቸውን ተአማኒ አድርገው ቢያቀርቡም፤ በእነርሱ ምክርና ድጋፍ

ስር ያሉ ሰዎች ሚስጥራቸው የሚባክን ከመሰላቸው የሚሰማቸውን በግልጽ ከመናገር መቆጠብ ይጀምራሉ።

- ያለግልጽነት ደግሞ የምክርና ድጋፍ አገልግሎት ሊታወቅ የሚገባውን የነገሩን ልብ በፍጹም አናገኝም።

ተሳታፊዎች ስም ሳይጠሩ ወይንም ነገሮችን በጥቀት ሳይዘረዝሩ ሚስጥር ባለመጠበቅ ብቻ የተፈጠረን መጥፎ ገጠመኝ እንዲናገሩ እድል ስጥ። ሁኔታው የተፈጠረው በሃሜት ምክንያት ነው? የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ በሚያበሳጭ መልኩ ሁኔታውን ለማስረዳት ተጠቅሞበት ነው? ወይንስ ይህን ሚስጥር የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ በሰልጣኙ ላይ የበላይ ለመሆን እንደመጠቀሚያ በማድረጉ ነው? እንዲህ ባለው ሁኔታ የሚስጥር ጠባቂነት ጉድለት በአሰልጣኙ እና ሰልጣኙ ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ ያሳድራል?

## ማጠቃለያ

ለዚህ ክፍለትምህርት የትኛው ሐሳብ በአስተሳሰባችሁ ላይ መልካም ተጽዕኖ አምጥቷል?



አንድ ፈቃደኛ ተሳታፊ በዚህ ክፍለ ትምህርት የተሸፈኑትን ዋና ዋና ነጥቦች እንዲጠቅስ እድል ስጥ።

ስለመልካምና መርዛማ የማማከርና ድጋፍ አገልጋዮች የተቀመጠውን መስፈርት ከተመለከታችሁ በኋላ በየትኞቹ አሳቦች ላይ መስራትና ራሳችሁን ማስተካከል እንዳለባችሁ ተገነዘባችሁ?



ለማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች፣ ለሰልጣኞች እና በመካከላቸው ሊኖር ስለሚገባው ምስጢር ጠባቂነት እና ተዓማኒነት እንዲሁም በማማከር እና ድጋፍ ሊኖር ስለሚገባው ንጹህ ህብረት ጸልዩ።

# ክፍል ትምህርት አራት

# የማማከርና ድጋፍ ህብረትን መጀመር

"ኢየሱስ ወደር የማይገኝለትን የማማከር እና ድጋፍ ሞዴል አዘጋጅቶ ተግብሮ ሰጥቶናል"
*–Teja & Osterhouse*






## ዓላማ

- በማማከርና ድጋፍ የሚኖርን ቃል ኪዳን መዘርዘር፡፡
- በማማከርና ድጋፍ ወቅት ሊኖር ሚገባን አጀንዳ ምሳሌ መስጠት፡፡
- በማማከርና ድጋፍ የሚያገለግለው ግለሰብ ሊጠቀምብት የሚችል ጥያቄዎችን ማዘጋጀት፡፡
- የትግበራ ነጥቦች አስፈላጊነትን ለማስረዳት፡፡
- የምክርና ድጋፍ አገልጋዩ መዝግቦ የሚያስቀምጠውን ሂደት እንዴት መጠቀም እንደሚገባ ለመማር፡፡

### የማማከርና ድጋፍ አገልጋዩ ቃልኪዳን

የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት በሶስት ቀለበት ነው፤ እግዚአብሔር፣ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ እና በማማከር እና ድጋፍ ስር የሚገኘው ሰልጣኝ፡፡ ይህ መንፈሳዊ ቃል ኪዳን ነው፡፡

የማማከርና ድጋፍ አገልጋዩ ቃልኪዳን







**የማማከርና ድጋፍ አገልግሎት ቃልኪዳን ግብአቶች**

1. የትና እንዴት እንገናኝ?
2. በስብሰባችን ምን ያህል ጊዜ መውሰድ ይገባዋል?
3. በየስንት ጊዜው እንገናኝ?
4. በምንገናኝበት ጊዜ የውይይታችን ርዕስ ምን መሆን አለበት?
5. ምን አይነት ነገሮች ናቸው ፊጽሞ እንዳይነሱ እንደነውር መውሰድ የሚገባን?
6. የተአማኒነት መመፈያችን ምን መሆን አለበት?
7. ስመስራት ያሰብነውንና ያቀድነውን አንዳሳካን እንዴት ልናውቅ እንችላለን?

## የማማከርና ድጋፍ አገልግሎት ቃልኪዳን ግብአቶች

የማማከር እና ድጋፍ ቃልኪዳን በዚህ አገልግሎት ውስጥ ለሚመሰረተው ህብረት መሰረት የሚሆኑ የመግባቢያ ህጎችን ለማወቅ መደላደል ይፈጥራል፡፡ ቃልኪዳኑ የሚከተሉትን ጥቄዎች ይመልሳል:-

* በማማከር እና ድጋፍ ስር ላሉ ሰልጣኞች በ MNM ስልጠና በመጨረሻው የቤተክርስቲያን ተከላ ስልጠና መርሃ ግብር ሞጁል ውስጥ እንደሚገኝ በመግለጥ ተወያዩ፡፡

1. የትና እንዴት እንገናኝ?

2. በስብሰባችን ምን ያህል ጊዜ መውሰድ ይገባዋል?

3. በየስንት ጊዜው እንገናኝ?

4. በምንገናኝበት ጊዜ የውይይታችን ርዕስ ምን መሆን አለበት?

5. ምን አይነት ነገሮች ናቸው ፈጽሞ እንዳይነሱ እንደነውር መውሰድ የሚገባን?

6. የተአማኒነት መመፈያችን ምን መሆን አለበት?

7. ለመስራት ያሰብነውንና ያቀድነውን አንዳላካን እንዴት ልናውቅ እንችላለን?



በአብዛኛው የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች እስካላመኑበት በዚህ አገልግሎት ውስጥ የጠለቀ ውይይት ማድረግ አይቻልም፡፡ በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ የማይናገራቸው የራሱ ገመናዎች ይኖሩታል በተለይ ደግሞ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ያለበት ቤተክርስቲያን መጋቢ ከሆነ፡፡

አንድ ጊዜ በማማከርና ድጋፍ የተገናኙ አገልጋይና ተማሪ ሲጀምሩ ያቀዱትን ካሳኩ በኋላ በራሳቸው ምርጫ የማማከርና ድጋፍ ህብረቱን በፈቃዳቸው መቀጠል ይችላሉ፡፡ በዚህ መልኩ ለመቀጠል ከወሰኑ አዲስ የቃልኪዳን ሰነድ መፈረም ይጠበቅባቸዋል፡፡

### የማማከርና ድጋፍ ቃልኪዳን ከመፈረማችን በፊት ልንጠይቃቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጥያቄዎች በአዋቂዎች ትምህርት መሰረት በእናንተ ምክርና ድጋፍ ስር ሲሆን የመረጠን ተማሪ መጠየቅ የምትችሏቸው ናቸው፡፡

| |
|---|
| 1. ለምንድን ነው በማማከርና ድጋፍ አገልግሎት ስር ለማለፍ የፈለግከው? |
| 2. ምንአይነት ክህሎት ወይንም ዕውቀት(መረጃ) ነው መማር የምትፈልገው? |
| 3. በሚቀጥሉት አምስት ወራት ውስጥ ምን አይነት ባህሪን ማዳበር ትፈልጋለህ? |
| 4. በሚመጡት ወራቶች ምን አይነት ባህሪያትን ማስወገድ ትፈልጋለህ? |
| 5. ከዚህ በፊት ያካበትከውና እግዚአብሔር ሊጠቀምበት የሚችል ምን አይነት ልምድ አለህ? |
| 6. በአሁኑ ወቅት ከቤተሰብም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ህብረት በተመለከተ ምን አይነት ችግሮች ወይንም ተግዳሮቶችን እየተጋፈጥክ ትገኛለህ? |



የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ በእርሱ ስር ላለ ሰልጣኝ ሊያቀርባቸው የሚገቡ ስድስቱን ጥያቄዎች አንብብላቸው፤ ከዚያም ከእነዚህ ጥያቄዎች በጠጨማሪ ሊጠየቁ ይገባቸዋል የሚሉትን ተሳታፊዎች

## ለማማከርና ድጋፍ የሚሆን አጀንዳ

የውይይት አጀንዳ መያዝ ለማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ልማት እንደልብ ማስተካከል እንዲቻል እድል ይሰጠዋል፡፡ ይሁን እንጂ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ የአጀንዳ ባሪያ መሆን አይገባውም፤ ምክንያቱም በእርሱ የማማከር እና ድጋፍ ስር የሚሰጥነው ግለሰብ አስቸኳይ እና ያልተጠበቁ አስፈልጎቶችን ይዞ ሊመጣ ስለሚችል፡፡



## ሶስቱ የማማከርና ድጋፍ ጥያቄዎች

በማማከርና ድጋፍ አገልግሎት ላይ የሚሰማሩ አገልጋይ በእርሱ ማማከርና ድጋፍ ስር ስለሚሰጥነው ሰው ሶስት መሰረታዊ የሕይወት ዘርፎች ግድ ሊሰው ይገባል፡፡







1. በምክርና ድጋፍ ስር ያለ ተማሪ መንፈሳዊ ሕይወት
2. ከቤተሰቡጋር ያለ ሕብረት
3. በምክርና ድጋፍ ስር ያለ ተማሪ የአገልግሎት ሕይወት

## መንፈሳዊ ሕይወት

በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለው ሰልጣኝ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ያልተቋረጠ ህብረት በአገልግሎቱ ለሚቀዳጀው ስኬት መሰረታዊ ነው፡፡ በማማከር እና ስልጠና ስር ለላለ ተማሪ መንፈሳዊ ሕይወት ቀዳሚውን ትኩረት ሊያገኝ ይገባል፤ ምክንያቱም ብዙ አገልጋዮች በቤት እና በአገልግሎት የወደቁት በመንፈሳዊ ድካም ነው፡፡ቤተክርስቲያን የመትከል ከበድ ያለ ጥሪ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር በጥብቅ ቁርኝት መጓዝን ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ነው የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች እነርሱ በሚያሰለጥኑት ተማሪዎች ውስጥ እግዚአብሔር የሚሰራውን እና የሚናገረውን ለመስማት ራሳቸውን መቃኘት የሚገባቸው፡፡

| በምክርና ድጋፍ የሚያገለግል ሰው ስለተማሪው መንፈሳዊ ሕይወት ሊጠይቅ የሚገባው ጥያቄዎች |
|---|
| •እግዚአብሔር በዚህ ወቅት ምን እየተናገረህ ነው? በምን አወቅህ?<br>•ካለፈው ስብሰባችን ወዲህ እግዚአብሔር ምን አስተማረህ?<br>•ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ህብረት (አካሄድ) በምን አይነት ሁኔታ ትመዝነዋለህ፤ በጣም ጥብቅ፣ መካከለኛ ወይንም ሩቅ?<br>•በየቀኑ እግዚአብሔርን ለማግኘት የጥሞና ጊዜ ትወስዳለህ? አስረዳ፡<br>•ቤተክርስቲያንን ስትተክል የጸሎትን እና የጾም ጸሎትን ልምምድ እንዴት አዋህደህ አቀረብክ? |



የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ሰልጣኙን ስለመንፈሳዊ ሕይወቱ ሊጠይቀው የሚገባውን ጥያቄዎች ምሳሌ በዝርዝር አቅርብ፡፡ ታዲያ እነዚህ እንደምሳሌ የተነሱ ጥያቄዎች በ www. multiplicationnetwork.org ላይ እንደሚገኝ አሳውቅ፡፡

**ማስታወሻ፡-** በምክርና ድጋፍ ስር ያለ ተማሪ የሚናዘዘው ኃጢአት ቢኖረው ራሱን የመግለጥ አለመግለጡ የሚወሰነው ሁለቱ ባላቸው መተማመን ላይ ነው፤ ሁለቱም መነሻቸው መተማመን እና ሕይወትን የሚለውጥ ምክር ላይ ሆኖ ውጤቱም በምክርና ድጋፍ ስር የሚገኘውን ተማሪ ሕይወት ወደነበረበት መመለስ መሆን አለበት፡፡ በማማከርና ድጋፍ የሚያገለግል ሰው በእርሱ ስር የሚሰጥነው ተማሪ ኃጢያቱን ለእግዚአብሔር እንዲናዘዝ ማበረታታት፤ በዚህም ኃጢአት ምን ያህል ጸያፍ እንደሆነ እንዲያውቅና የሰራውን መጥፎ ተግባር የሚክስ መልካም ስራ እንዲከውን ማስቻል ይጠበቅበታል፡፡

በማማከርና ድጋፍ ስር ስሳለ ተማሪ መንፈሳዊ ሕይወት ሊጠየቅ የሚገባ ተጨማሪ ጥያቄ፡

## የቤተሰብ ሕይወት

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች በእነርሱ ስር የሚሰጥኑ ተማሪዎችን ከትዳር አጋሮቻቸው እና ከልጆቻቸው ጋር ስላላቸው ህብረት የሚያውቁበትን ጥያቄ መጠየቅ ይገባቸዋል፡፡ ታዲያ ይህን በሚያደርጉበት ወቅት በጣም ጥንቃቄ መውሰድ እና በተገቢው

ተሳታፊዎች በእነርሱ የማማከር እና ድጋፍ ስር ያለን ተማሪ ስለ ቤተሰብ ሕይወት ለመጠየቅ ነጻነት ይሰማቸው እንደሆን ጠይቅ፡፡ ምን ሌነት ጥያቄዎችስ ናቸው ተቀባይነት ያላቸው? የትኞቹስ ናቸው ነውር የሚሆኑ ጥያቄዎች?

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች ሊያልፉት የማይገባ የአሳብ ወሰን ምን ሊሆን ይችላል? ተሰታፊዎችን ሁለት ወይም ሶስት እየሆኑ ስለቤተሰብ ሕይወት ሊጠየቁ የሚገባቸውን ጥያቄዎች ዝርዝር እንዲጽፉ እድል ስጥ፡፡ ታዲያ ይህን ተግባር ለማጠናቀቅ 15 ደቂቃ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ከዚያም የዘረዘሯቸውን ጥያቄዎች በሰሌዳ ወይንም በትልቅ ወረቀት ላይ አስፍር፡፡

መንገድ መያዝ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ይህ ከልብ ለሚታመን ወዳጅ የሚነገር ስለሆነ፡፡ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት በስራችን ያለውን ተማሪ የምንጠቀምበት እንጂ የምንገዳበት አይደለም፡፡ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ለተማሪው የቤተሰብ ጉዳይ የሚጠይቀው ለመጸለይ በተዘጋጁበት ሰአት ሳይሆን፤ ከዚህ ይልቅ ተማሪው ስለቤተሰቡ የደስታ እና የመከራ ወይም ስደት የሚያወሩበት እድል ሲሰጠው ይገባል፤ ነገር ግን ተማሪው ስለቤተሰቡ የሚያወሩበት ከባቢ እና ገመና ሽፋኝነት ያለምንም ስጋት እንዲናገር የሚጋብዘው ሲሆን ይገባል፡፡

| በምክርና ድጋፍ የሚያገለግል ሰው ስለተማሪው የቤተሰብ ሕይወት ሊጠይቅ የሚገባው ጥያቄዎች |
|---|
| • ምን ያህል ጊዜ ስቤተሰብህ ትሰጣለህ?<br>• ባለቤትህና አንተ በየሳምንቱ ከሁሉም ነገር ነጻ የሆነ ለሁለታችሁ ብቻ የለያችሁት አንድ ቀን አላችሁ? ቀኑን እንዴት እንደምታሳልፉት ንገረኝ፡፡<br>• ለልጆችህ ስለምትሰጠው ጊዜ ልጆችህ ምን ይሰማቸዋል?<br>• ቤትህ የሰማይ ነጸብራቅ የሆነ ሰላም እንዲኖረው ምን አይነት ጥረቶች ታደርጋለህ? እንዴት ነው ቤትህ የህዝብ ቤት እንዳይሆን በየጊዜው የሚመጡ ተማሪዎችህን መጠን እና የሚመጡበት የጊዜ ርቀት እንዴት አድርገህ ትወስናለህ?<br>• የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎትህን ያስተጓጉላል ብለህ ያመንክበትን ከቤተሰብ ጋር የተያያዘ ጉዳይ አለ? |

በማማከርና ድጋፍ ስር ላለ ተማሪ የቤተሰብ ሕይወት ሊጠየቅ የሚገባ ተጨማሪ ጥያቄ

______________________________

______________________________

______________________________

## የአገልግሎት ሕይወት

ምንም እንኳን የዚህ ስልጠና የመጨረሻ ግቡ የጤናማ ቤተክርስቲያናትን መተከል ማረጋገጥ ቢሆንም፤ ከላይ ያነሳናቸው ጥያቄዎች ደግሞ እንዴት ጤናማ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይን ማሰንበት እንደሚቻል የሚዳስሱ ናቸው፡፡ መንፈሳዊ ሕይወት እና የቤተሰብ ሕይወት ከቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ጋር ድርና ማግ (ሊለያዩ የማይችሉ/ የተሳሰሩ) ናቸው፡፡

ስዚህም ነው በቀድሚያ በዚህ ክፍለ ትምህርት እነዚህን ሁለት ጉዳዮች የምንዳስሰው። ስለቤተክርስቲያን ተከላ የሚጠየቀው ጥያቄ በሶስተኛነት የመጣው ከዚህ የተነሳ ነው። የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ አሳብ ከአገለልግሎቱ ሊርቅ የሚችለው በቀድሚያ መንፈሳዊ ሕይወቱን እና የቤተሰብ ሕይወቱን በሚመለከት በቂ ጊዜ ሳይወስድ ሲቀር ነው።

**በምክርና ድጋፍ የሚያገለግል ሰው ስለተማሬው የአገልግሎት ሕይወት ሊጠይቅ የሚገባው ጥያቄዎች**

- በቀርብ የተዋወቅኸውን ሰው መቼ እንደጎበኘኸው ታስታውሳለህ? እንዴት ነበር ጉብኝቱ የተደረገው? ለምን?
- ቤተክርስቲያን በመትከል ሂደት ውስጥ አሁን ትግል እየሆነብህ ያለ ነገር ምንድን ነው? ስለጉዳዩ አጫውተኝ።
- ባለፈው ከተገናኘን ጀምሮ ምን ያህል ጉብኝቶችን አደረግህ? ካደረካቸውስ ጉብኝቶች ምን ያህሉቹ የጀመርካቸውን ስራዎች ለመከታተል አሳማን ማዕከል ያደረጉ ናቸው?
- የምትጎበኘውን አካባቢ በበለጠ ለማወቅ ምን እያደረግህ ነው?
- ለቤተክርስቲያን ተከላ ስለመረጥከው አካባቢ ምንአይነት አዳዲስ ነገሮች ተምረሃል?
- አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በማቋቋሙ ረገድ ምንያህል ተሳክቶልሃል?
- የተገለጡ አለመግባባቶች አሉ? ካሉ እንዴት አድርገህ ፈታሃቸው?
- ከመሰረትካቸው አነስተኛ የሰው ቁጥር ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ተሳታፊዎች ውስጥ ወደ ፊት መሬ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች እንዳሉ አስተውለሃል? ስላስተዋልካቸው ሰዎች ግለጽ።
- ቤተክርስቲያን እየተተከለች ያለበት ፍጥነት ምን ያህል ትርጉም ይሰጥሃል?
- ከቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ የትኞቹ የአገልግሎት ዘርፎች በትክክል ስለማይከወኑ ምቾት ነስተውሃል የትኞቹንስ አንተ ልታስተካክል ትችላለህ?
- አሁን ልትተክል ላሰብከው አጥቢያ በጸሎት አብረውህ እንዲቆሙ የጠየካቸው ሰዎች እነማን ናቸው? በምንያህል የጊዜ ርቀት የጸሎት ርዕስህን እና የጸሎት መልስህን መቀበልህን ታሳውቃቸዋል?

ተሳታፊዎች በማማከር እና ድጋፍ የሚያገለግለው ግለሰብ በስልጠናው ወቅት ሊያስተላልፈው የሚገባ ዕውቀት እና ክህሎት ምን እንደሆነ እንዲጠቁሙ ዕድል ስጥ። የሚሰጡህን አሳብ በሰሌዳ ዌንም በትልቅ ወረቀት ላይ

በማማከርና ድጋፍ ስር ስላለ ተማሪ የአገልግሎት ሕይወት ሊጠየቅ የሚገባ ተጨማሪ ጥያቄዎች

ለምን ይመስልሃል በዚህ ስልጠና የመንፈሳዊ ሕይወትና የቤተሰብ ሕይወት ከአገልግሎት ሕይወት በፊት አብይ ጉዳይ ሆነው የቀረቡት?



## የትግበራ ነጥቦች

የማማከርና ስልጠና አገልግሎት "ቀጣይ እቅድህ መንድን ነው?" የሚለውን ይህን ጥያቄ የምናማክረውንና የምንደግፈውን ተማሪ ካልጠየቅን ሙሉ አይሆንም፡፡ በማማከርና ድጋፍ ውስጥ ያለ ተማሪ በቀጣይ ምን እንደሚያስብ ለማወቅ እንዲህ ባለው ጥያቄ ወደፊቱን ያስብ ዘንድ ሲበረታታ ያስፈልጋል በዚህም ስለመንፈሳዊ ሕይወቱ፣ የቤተሰብ ሕይወቱ እና የቤተሰብ ሕይወቱ ሳይም ይሰራ እንደሆን መጠየቅ ይገባዋል፡፡

| በማማከርና ድጋፍ የሚያገለግል ሰው ሊጠየቅ የሚገባው ጥያቄ |
|---|
| • አሁን ያለውን ሁኔታ በተመለከተ ምን አይነት እርምጃ ለመውሰድ አስበሃል? |
| • ዛሬ ከተገናኘንበት እስከመጪው የውይይት ጊዜአችን ምን ለማከናወን አቅደሃል? |
| • አሁን ያለንበትን ሁኔታ በተመለከተ በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለብህ አስበሃል? |
| • በ(ስም) እና (ስም) መካከል የተፈጠረን አለመግባባት በምንአይነት መንገድ እፈታዋለሁ ብለህ ተስፋ ታደርጋለህ? |
| • አሁን ከገጠመህ ችግር አሻግረህ ምትመለከተው ተስፋ አለህ? |
| • ዛሬ ከተገናኘንበት እስከ ሚቀጥለው የውይይት ጊዜአችን የቤተክርስቲያን ተከላን ያሳልጣሉ ብለህ ያሰብካቸው ሶስት ነገሮች ምን ምን ናቸው? |
| • በሚቀጥለው ከ(ስም) ጋር ሳምንት ውይይት ለመጀመር ምን ታደርጋለህ? |
| • በእርግጥ ያወቅኸውን ችግር ለመፍታት ወዴት ወይንም ወደማን ትሄዳለህ? |

## ከትግበራ ነጥብ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## ልምድ ያላቸው ሰዎች ጥቅም

ከጊዜ ወደጊዜ የማማከር እና ድጋፍ ስራን በምንሰተበት ወቅት አንድ የምንገነዘበው በእኛ ስር የሚሰጥነው አገልጋይ ከአእምሮአችን በላይ የሆነ ጉዳይ ሲገጥመው እንደሚችል ነው። እንዲህ በሚሆን ጊዜ ሰልጣኞችን ከሌሎች ሰዎች ምክር እና ድጋፍ እንዲያገኙ ማበረታታት ያስፈልጋል። በእርግጥ በሁሉም የሕይወት መስክ ልምዳችን የዳበረ ባላሙያዎች መሆን ስለማንችል፤ መልካም የማማከር እና ድጋፍ አሰልጣኞች ከሆንን አንዳንድ ጊዜ ከእኛ አቅም በላይ በሆነው ገጠመኝ ላይ በሙያው ልምድ ያላቸው ሰዎች እንዲያማክሩት ሰልጣኞችንን ወደእነዚህ ሰዎች እንልካለን። ይህም ለቀጣይ የማማከር እና ስልጠና ሂደት ጥሩ ግብአት ይሆነናል። አሰልጣኙ ሰልጣኙን እንዲህ ብሎ ሊጠይቅ ይችላል "ከ....ጋር በነበረህ ቆይታ ባለፈው የጠየቅኸውን ጥያቄ ለመመለስ እንዴት ረዳህ? በዚያ ጉዳይ ልታካፍለኝ የምትፈልገው ነገር አለ?"

1. በማማከርና ድጋፍ የሚያገለሉ ሰዎች ያለባቸውን <u>ውስንነት</u> ማወቅ ይኖርባቸዋል።




በማማከርና ድጋፍ አገልግሎት ውስጥ ከተሰማሩ አገልጋዮች ጥቂቶቹ የማማከር ስልጠና የወሰዱ ሲሆን በዚህም ከተሰመደ ምክር ከፍ ያለ የማማከር አቅም ያላቸው ቢሆንም በዚህ መስክ ሙሉ ጥናት ስላላደረጉ በማማከሩ ረገድ ያለባቸውን ውስንነት ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። ስለሆነም በእነርሱ ምክርና ድጋፍ ስር ያለን ሰው መቼ በሙያው ልምድ ወዳላቸው ግለሰቦች መላክ እንዳለበት ማወቅ ይጠበቅበታል። ይህን ሳያደርግ ቢቀር በእርሱ የማማከርና ድጋፍ ስር ያለን ግለሰብ መጉዳት ብቻ ሳይሆን እንደየ ሁኔታው፤ ችግሩን እያወቁ ወደ ህክምና አለመላክ እንደየ ሁኔታው በህግ የሚያስጠይቅ ነው።

ተሳታፊዎች ከዚህ በፊት ተምረውት በማያውቁት እና በዚህ ክፍለትምህርት ባገኙት ዕውቀት መሰረት ምን ሊከውኑ እንዳሰቡ እንዲጽፉ አድርግ። ከዚያም ጥቂት ተሳታፊዎች የጻፉትን ለጠቅላላው ተሳታፊ እንዲያቀርቡ እድል ስጥ።

2. በማማከርና ድጋፍ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ምቹት ባልሰጣቸው እና ብቁ እንዳልሆኑ በሚያስቡት ጉዳይ ላይ ጥልቅ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች (ስፔሻሊስትስ) እርዳታቸውን ለማግኘት መጋበዝ አለበት። በዚህም በእርሱ የማማከርና ድጋፍ ስር የሚገኙ ተማሪዎች ከሌሎች ጋር የመተዋወቅ እና እርዳታ የሚያገኙበት ምህዳር ይሰፋል። እንዲህ ያሉ በሙያቸው የበቃ ልምድ ያላቸውን ሰዎች በማማከርና ድጋፍ የሚያገለግለው አገልጋይ በእርሱ ስር ለሚሰለጥኑ ተማሪዎች ማስተዋወቁ፤ እርሱ አገልግሎቱን በፈጸመ ወቅት ተማሪዎቹ ባለሙያው ባገለገለበት ጉዳይ ላይ የእነርሱ አማካሪ ደጋፊ ሊሆን ይችላል።

## የማማከርና ድጋፍ አገልጋዩ የመከታተያ ቅጽ

በማማከርና ድጋፍ አገልጋዩ የመከታተያ ቅጽ ላይ መቼ ከተማሪዎቻቸው ጋር እንደተገናኙ፣ ምን እንደተወያዩ እና ምን አይነት የትግበራ እቅድ እንዳወጡ ይመዘግብበታል። በዚህ ቅጽ ላይ በውይይት ወቅት አይጻፍም ይልቁንም ልክ ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚያደርጉት ውይይት እንዳበቃ መዝግቦ የሚይዝበት ዶሴ ነው።

ቀጣዩን ውይይት ከማድረጋቸው በፊት በማማከርና ድጋፍ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ከዚህ ቀደም የተወያዩትን ሁሉ ከመከታተያ ቅጹ ላይ መከለስ ይገባቸዋል። ይህም ብቻ ሳይሆን ከመከታተያ ቅጹ ቀጥሎ ያለው ገጽ ላይ በቀጣይ በየትኛው አጀንዳ ላይ መወያየት እነዳለባቸው ለመጠቀም የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በእነርሱ ምክርና ድጋፍ ስር ያለን

ተማሪ የሚጠቅሙ ስለሆኑ እነዚህን በክፍለ ትምህርቱ ወቅት መጠየቅ አስፈላጊ ነው። የማማከርና ድጋፍ አገልጋዩ የመከታተያ ቅጽ በሚቀጥለው ክፍል እናገኛለን።




## መደምደሚያ

ከዚህ በፊት አስበህ የማታውቀው በዚህ ክፍለትምህርት ያገኘኸው አዲስ ነገር ምን እንደሆነ ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ አስፍር።

## የማማከርና ድጋፍ አገልጋዩ መከታተያ ቅጽ

በምክርና ድጋፍ ስር ያለ ተማሪ ስም______________________________

ውይይቱ የሚደረግበት ቀን____ /____ /____ ሰዓት_____ :_____ቦታ______________

**የመነሻ ጥያቄዎች፡** ከቀደመው ሞጁል ምን ተማራችሁ? እንዴትስ እየተገበርከው ትገኛለህ? መንፈሳዊ ሕይወትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች (ምሳሌ የሚሆኑ ጥያቄዎች በስተጀርባ ተዘርዝረዋል፡፡)

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

የቤተሰብ ሕይወትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች (ምሳሌ የሚሆኑ ጥያቄዎች በስተጀርባ ተዘርዝረዋል፡፡)

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

የአገልግሎት ሕይወትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች (ምሳሌ የሚሆኑ ጥያቄዎች በስተጀርባ ተዘርዝረዋል፡፡)

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

**ሁልጊዜ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ፡-የ ሀ.ስ.መ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽህን አገልግሎቱን ሚመራው ሰው አሳይተሃል?**

**የትግበራ ደረጃዎች፡-** (ይህንኛውን ክፍል በምክርና ድጋፍ ከምታገለግለው ተማሪ ጋር በመሆን ሙላ)

**መንፈሳዊ ሕይወትን የተመለከቱ ጥያቄዎች**

- እግዚአብሔር በዚህ ወቅት ምን እየተናገረህ ነው? በምን አወቅህ?
- ከባለፈው ስብሰባችን ወዲህ እግዚአብሔር ምን አስተማረህ?
- ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ህብረት (አካሄድ) በምን አይነት ሁኔታ ትመዝነዋለህ፤ በጣም ጥብቅ፣ መካከለኛ ወይንም ሩቅ?
- በየቀኑ እግዚአብሔርን ለማግኘት የጥሞና ጊዜ ትውዳለህ? አስረዳ፡፡
- ቤተክርስቲያንን ስትተክል የጸሎትን እና የጾም ጸሎትን ልምምድ እንዴት አዋህደህ አቀረብክ?
- የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት በግል የጥሞና ጊዜ ትወስዳለህ? አስረዳ፡፡
- ምናልባት መናገር ትፈልግ እንደሆን በመንፈሳዊ ሕይወትህ ያለብህን ተግዳሮቶች አሳየን፡፡

## ቤተሰብን የተመለከቱ ጥያቄዎች

- ምን ያህል ጊዜ ለቤተሰብህ ትሰጣለህ?
- ባለቤትህና አንተ በየሳምንቱ ከሁሉም ነገር ነጻ የሆነ ለሁለታችሁ ብቻ የለያችሁት አንድ ቀን አላችሁ? ቀኑን እንዴት እንደምታሳልፉት ንገረኝ፡፡
- ለልጆችህ ስለምትሰጠው ጊዜ ልጆችህ ምን ይሰማቸዋል?
- ቤትህ የሰማይ ነጸብራቅ የሆነ ሰላም እንዲኖረው ምን አይነት ጥረቶች ታደርጋለህ? እንዴት ነው ቤትህ የህዝብ ቤት እንዳይሆን በየጊዜው የሚመጡ ተማሪዎችህን መጠን እና የሚመጡበትን የጊዜ ርቀት እንዴት አድርገህ ትወስናለህ?
- የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎትህን ያስተጓጉላል ብለህ ያመንክበትን ከቤተሰብ ጋር የተያያዘ ጉዳይ አለ?

## አገልግሎትን የተመለከቱ ጥያቄዎች

- በቅርብ የተዋወቅኸውን ሰው መቼ እንደጎበኘኸው ታስታውሳለህ? እንዴት ነበር ጉብኝቱ የተደረገው? ለምን?
- ቤተክርስቲያን በመትከል ሂደት ውስጥ አሁን ትግል እየሆነብህ ያለ ነገር ምንድን ነው? ስለጉዳዩ አጫውተኝ፡፡
- ባለፈው ከተገናኘን ጀምሮ ምን ያህል ጉብኝቶችን አደረግህ፤ ካደረካቸው ጉብኝቶች ምን ያህሉቹ የጀመርካቸውን ስራዎች ለመከታተል አላማ የነበሩቸው ናቸው?
- የምትጎበኘውን አካባቢ በበለጠ ለማወቅ ምን እያደረግህ ነው?
- ለቤተክርስቲያን ተከላ ስለመረጥከው አካባቢ ምንአይነት አዳዲስ ነገሮች ተምረሃል?
- አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በማቋቋሙ ረገድ ምንያህል ተሳክቶልሃል?

- የተገለጡ አስመግባባቶች አሉ? ካሉ እንዴት አድርገህ ፈታሃቸው?
- ከመሰረትካቸው አነስተኛ የሰው ቁጥር ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ተሳታፊዎች ውስጥ ወደፊት መሪ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች እንዳሉ አስተውለሃል? ስላስተዋልካቸው ሰዎች ግለጽ፡፡
- ቤተክርስቲያን እየተተከለች ያለበት ፍጥነት ምን ያህል ትክክል ነው ብለህ ታስባለህ?
- ከቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ የትኞቹ የአገልግሎት ዘርፎች በትክክል ስለማይከወኑ ምቾት ነስተውሃል የትኞቹንስ አንተ ልታስተካክል ትችላለህ?
- አሁን ልትተክል ላሰብከው አጥቢያ በጸሎት አብረውህ እንዲቆሙ የጠየካቸው ሰዎች እነማን ናቸው? በምን ያህል የጊዜ ርቀት የጸሎት ርዕስህን እና የጸሎት መልስህን መቀበልህን ታሳውቃቸዋል?

## የትግበራ ነጥቦች

- አሁን ከገጠመህ እንቅፋት እንዴት እወጣለሁ ብለህ ተስፋ ታደርጋለህ?
- ወዴት (ወደ ማን) በመሄድ የገለጥከውንና የገጠመህን ለየት ያለ ችግር ትፈታለህ?
- ከዛሬ ስብሰባችን እስከሚቀጥለው የውይይት ጊዜአችን ባለው የጊዜ ክፍተት ምን ለመከወን አስበሃል?
- አሁን ያለህበትን ሁኔታ በተመለከተ በቀጣይ ማድረግ ያብህ ምን እንደሆነ ተገንዝበሃል?

# ለማስተማር የተዘገጀ ታሪክ/ድራማ

# ለማማከርና ድጋፍ አገልግሎት የተዘጋጀ

## አላማው

የዚህ ተግባራዊ ልምምድ አላማ ተሳታፊዎች ስለማማከርና ድጋፍ አገልግሎት ምንነት የሚረዱበትን እድል ለመፍጠር ነው፡፡ ለዚህም ልምምድ ይረዳን ዘንድ ሶስት የተለያዩ ለማስተማር የተዘጋጁ ታሪኮችን ያቀረብን ሲሆን፤ ለእያንዳንዱ አስር ደቂቃ የሚፈጅ የውይይት ጊዜ መድበናል፡፡ እያንዳንዱ ታሪክ የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ እና በማማከርና ድጋፍ ስር ያለ ተማሪ እንዲኖረው ሆኖ የሚተውን ሰው ያስፈልጋል፡፡ ለእነዚህ ሰዎች ታሪኩን ከነገርናቸው በኋላ ለሌሎች ከማቅረባቸው በፊት ለብቻቸው የሚያጠኑበትን ጊዜ ስጧቸው፡፡ ከዚያም የቀረበው "ድራማ" እንዳለቀ ተመልካቾች የምክርና ድጋፍ አገልጋይ ሆኖ የተወነው ሰው የሰጠው መፍትሄ አጥጋቢ መሆን አለመሆኑን እንዲመዝኑና እንዲናገሩ እድል ስጧቸው፡፡ ምንድን ነው አገልጋዩ በሚገባ የከወነው? ውጤቱን የተሻለ ለማድረግ ምን ማድረግ ነበረበት?

## አስተያየት

በድራማው ወቅት የምክርና ድጋፍ አገልጋዩ ከጠቅላላው የውይይት ጊዜ ምንያህሉን እንደተጠቀመ አስተውሉ፡፡ አነስተኛውን ጊዜ መውሰድ ያለበት አገልጋዩ ነው፡፡ ከዚህ በተረፈ የእርሱ ድርሻ መሆን ያለበት የራሱን መላምት ከመናገር ይልቅ ተማሪውን መጠየቅ የተግባቦቱ መሰረት መሆን ያለበት፡፡ አገልጋዩ፡-

1. ሁኔታውን ለመረዳት የሚያግዙ ጥያቄዎች መጠየቅ ይገባዋል፡፡
2. የሚያገለግለው ተማሪ የሚናገረውን በመድገም ሁኔታውን በትክክል መረዳቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
3. ተማሪው ራሱ መፍትሄዎችን እንዲያመጣ የሚያግዙ ጥያቄዎችን መጠየቅ ተማሪው ራሱ ችግሮችን እንዲፈታ መንገድ ይሆኑታል፡፡
4. ለተማሪው ርህራሄ ሲሰማውና የሚናገረውን ለመስማት ፍላጎት ሲያሳይ ነው፡፡

**ማስታወሻ፡- ምንጊዜም ወንድ ወንድን ሴት ደግሞ ሴትን ብቻ ነው ማማከርና መደገፍ ያለበት፡፡**

ታሪክ 1

አንድ ተማሪ በማማከርና ድጋፍ ያገለግለው ወደነበር አገልጋይ በፍርሃትና በጥድፊያ ይመጣል፡፡ እንዲህ በጥድፊያ ያመጣው ጉዳይ ደግሞ፤ ከሳምንት በፊት እርሱ ይመራው በነበረ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ውስጥ ያሉ ሁለት ሰዎች ኃይለቃል እስከመነጋገር የደረሰ አለመግባባት ውስጥ ገብተው ነበር፡፡ ታዲያ ተማሪው የሰዎቹ ግጭት በዚሁ ከቀጠለ የጥናት ቡድኑንና እነርሱን ለመድረስ የተደረገውን ጥረት ሊያጠፋ፣ በህብረት መካከል መለያየትን ሊፈጥር እንዲሁም የወንጌሉን ቃል ሰዎች እንዳይሰሙ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ የተማሪው ስጋት እነዚህ ሁለት ሰዎች ተቃርኖ እነርሱን ብቻ ሳይሆን የቡድኑን አባላት ሁሉ እንደሚጎዳ ያምናል፡፡

ታሪክ 2

በማማከርና ድጋፍ የሚያገለግለው ግለሰብ ተማሪውን ስለቤተሰቡ ሲጠይቀው፤ ተማሪው ያለምንም መደበቅ ባለቤቱ የቤተክርስቲያን ተከሳ አገልግሎቱን እንደማትስማማበት ይነግረዋል፡፡ አገልጋዩም ተማሪው ከቻለ እንዴት አድረጎ የባለቤቱን ሐሳብ ለምን እና እንዴት መቀየር እንደሚችል ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ይሞክራል፡፡

ታሪክ 3

የማማከርና ድጋፍ አገልጋዩ ተማሪውን ስለመንፈሳዊ ሕይወቱ ይጠይቀዋል፡፡ ተማሪውም በቤተክርስቲያን አገልግሎት ጊዜው ስለተጣበበ በግል የጥሞና ጊዜ ማግኘት እንዳልቻለ ይናገራል፡፡ በዚህም ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደሌለው ያምናል፡፡

# የቤተክርስቲያን ተከላ ሪፖርት

ወርሃዊ ሪፖርት

## ጠቅላላ መረጃ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሪፖርቱ የተደረገበት ወር | | የምክርና ድጋፍ አገልግሎቱ ተከናውኗል | አዎን | የለም |

| | |
|---|---|
| የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ስም | |
| ቤተክርስቲያኒቱን የሚተክለው ሰው አካባቢ | |
| የአካባቢው አስተባባሪ | |

| ግለሰቦች | ወርሃዊ ግብ | ወርሃዊ ውጤት |
|---|---|---|
| በቅርቡ የተዋወካቸው ሰዎች<br>ቤተክርስቲያን ለመትከል ታስቦ ወንጌልን ለማድረስ የተዋወካቸው ሰዎች | | |
| ወደጌታ የመጡ አዳዲስ ሰዎች<br>የኢየሱስ ተከታዮች | | |
| በቅርብ የተጠመቁ ሰዎች<br>በጥምቀት ስርአት የተሳተፉ ሰዎች | | |
| በስልጠና ላይ ያሉ አዳዲስ መሪዎች<br>ለቤተክርስቲያን ተከላ የሚመለመል ሰው ለመሪነት የሰለጠነ ነው | | |

**አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የሚሳተፉበት ቡድን|** በትንሹ ሁለት ደቀመዝሙር እና አንድ መሪ

| | ወርሃዊ ግብ | ወርሃዊ ውጤት |
|---|---|---|
| አዳዲስ ትናንሽ ቡድኖች<br>በዚህ ወር የተጀመሩ ቡድኖች | | |
| በትናንሽ ቡድኖች የተካተቱ አዳዲስ ተሳታፊዎች<br>በዚህ ወር በትናንሽ ቡድኖች መሳተፍ የጀመሩ አዳዲስ ሰዎች | | |
| የቡድን መሪ የሆኑ አዳዲስ መሪዎች<br>በቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ክትትል የሚደረግለት ቡድን መሪ የሆነ አዲስ መሪ | | |

## የጸሎት ርዕስ

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________

## ምስክርነት

ከዚህ በታች ያለው ክፍት ቦታ የመጨረሻ ሳይሆን እንደመነሻ የቀረበ ሲሆን ተጨማሪ ወረቀት መጠቀም ይቻላል

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

# የጸሐፊያኑ ማስታወሻ

በዚህ መምሪያ ውስጥ ያልተካተቱ እና በዋናው/ኦርጂናሉ/ የአሰልጣኙ መምሪያ ውስጥ የሚገኙ የማብራሪያ ማስታወሻዎች በዚህ አባሪ ላይ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ከብዙ የምስክ ተሞክሮ ጥናት በኋላ በዚህ ይካተቱ የነበሩ ጭብጦች ተቀንሰው፣ የይዘት ቀደም ተከተሎች ትምህርቱን ተገቢነት ባለው የአሳብ ፍሰት ለማስተማር ያስችል ዘንድ እና እንደየአስፈላጊነቱ ለማስተካከል አዲያመች መጠነኛ ማስተካከያ ተደርጎባቸው ቀርበዋል፡፡ "የጸሐፊያኑ ማስታወሻ" በሚለው ክፍል ያሉት አሳቦች አንዳንድ ክፍለትምህርቶችን በበለጠ ጥልቀት ለማስተማር የሚረዱ አሳቦችን ስለያዘ፤ በቂ የስልጠና ጊዜ ካለ እነዚህን መጠቀሙ እጅግ መልካም ነው፡፡

## የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ክዋኔ ሂደት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች

ከተሳታፊዎች ጋር በመሆን የክሊንተንን እና የስታንሊን የአማካሪ እና ደጋፊ ትርጓሜ ቁልፍ ጭብጦችን ከለሱ፡- (1) ማማከር እና ድጋፍ አገለግሎት ሕብረትን መሰረት ያደረገ ነው (2) ያማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ የሚያካፍለው ልምድ አለው (3) አንድ ነገር ከአንዱ ወደ ሌላው ይተላለፋል (4) የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ እድገትን ያሳልጣል እንዲሁም (5) የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ያስታጥቃል፡፡ እነዚህን ይዘቶች እንደ መዋቅር በመጠቀም ከዚህ በታች የቀረበውን የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን አንድ በአንድ ገምግመው፡፡ ለእያንዳንዱ ምሳሌ የተሚላ ማብራሪያ በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት መርጃ መሳሪያ ግብአት ውስጥ *የቤተክርስቲን ተከላ አገልጋዩን ለምን በማማከር እና ድጋፍ እናገለግላለን?* በሚለው ክፍል እናገኛለን፡፡

## የማማከር እና ድጋፍ ስነ መለኮታዊ መሰረት

ይህ ርዕስ በሶስት የተከፈለ ነው፤ በመጀመሪያው ክፍል፤ ተሳታፊዎች እግዚአብሔር በስሉስ አሃድነቱ በሰዎች መካከል ስላለ ህብረት እንዴት መሰረት ሊሆን እንደሚችል ይመረምራሉ፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ፤ ከላይ ያነሳነው መርህ እንዴት እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩ ጋር ሲሄድ እንደሚችል ያሳያል፡፡ ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የክርስቶስ በስጋ መምጣት/ተሰግዎ/ን በመመርመር፤ ከዚህ የምናገኘው መርህ እንዴት ከማማከር እና ድጋፍ ጋር ሊያያዝ እንደሚችል ያመለክተናል፡፡

በስሉስ አሃድ በሆነው እግዚአብሔር ባህርይ ውስጥ የምናገኘው መሰረት

በዚህ ክፍል ደግሞ ተሳታፊዎች የእግዚአብሔር ስሉስ አሃድነት የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮችን

በማማከር እና ድጋፍ ከምናደርገው አገልግሎት ጋር በምን ይዛመዳል፡፡ በመጀመሪያ፤ እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ የገለጠበት ትክክለኛ መወከያ እንደሆነ ያብራራልናል፡፡

ምንም እንኳን ስላሴ የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባናገኘውም፤ የስሉስ አሃድነት እውነት ግን ከተለያዩ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ወደዚህ እውነት የሚያደርሱን አሳቦችን ማግኘት እንችላለን፡፡ ቤተርስቲያን ይህን ስያሜ ያጸደቀችው እግዚአብሔር ራሱን በ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ እንደገለጠ ለማስረዳት ነው፡፡

ሁለተኛ፤ ስሉስ አሃድ በሆነው መለኮት በእኩልነት የሚተካከሉ የሆኑ፣ እኩል ዘላለማዊ እና የማይነጣጠሉ አካላት ውስጥ ስላለ ፍጹም አንድነት እና ህብረት ተጨማሪ አስረጂ ነው፡፡ ይህን የስላሴ አካላት ህብረት ለማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት በሚከተሉት መንገዶች እንደ ትምህርት ተወስዶ ሲተገበር ይችላል፡፡

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር **ፍቅር** ነው፡፡ የእግዚአብሔር ባህርይ መገለጫ ቁልፉ ራስን አሳልፎ እስከመስጠት የሚደርስ ፍቅር ነው፡፡
- ሁለተኛ፤ ስሉስ አሃድነት ዘላለማዊ በሆነ በፍቅርና ህብረት የሚገለጥ **ማህበር** ነው፡፡
- ሶስተኛ፤ እግዚአብሔር በስሉስ አሃድነቱ ውስጥም ሆነ ከፈጠረው ፍጥረት ጋር **ህብረት** ለማድረግ ምሉዕ ነው፡፡
- አራተ፤ እግዚአብሔር ለሰዎች እና ለመላ ፍጥረቱ **ይጠነቀቃል**፡፡

እነዚህ የእግዚአብሔር ባህርያት መገለጫዎች እርሱ በፈጠረው ሰው ላይ ይንጸባረቃል፡፡

**ተግባር፡-**

የእግዚአብሔር ባህርይ በፍጥረቱ ላይ እንዴት እንደሚንጸባረቅ ተሳታፊዎች ምሳሌ እንዲሰጡ ጠይቅ፡፡ እንዴትስ ነው የእግዚአብሔር ባህርያት ከማማከር እና ድጋፍ አገልግሎታችን ጋር የሚዛመዱት?

## በእግዚአብሔር ፍጥረት ሲገለጥ

የእግዚአብሔር ባህርይ እና መገለጫ በእርሱ የመፍጠር ተግባር ውስጥ ተገልጧል፡፡ ለህብረት ያለው ፍቅር እና ችሎታ አጽናፈ ዓለምን እንዲፈጥር ከማነሳሳቱም በላይ ፍቅሩን እና እንክብካቤውን የሚያሳይበት መድረክ አድርጎ ተጠቅሞበታል፡፡ የሚታዩትን ዓለማት በሙሉ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣው ለራሱ ክብር እና ደስታ ነው፡፡ ተፈጥሮ እግዚአብሔር ለሰራው እና ላኖረው ፍጥረት ያለውን ትኩረትና መልካምነት ያሳያል፡፡ የሚያደርገውን ሁሉ የሚያደርገው ሌሎችን ለመጥቀም ነው፡፡ ይህን የባህርይ ማሳያ ለማረጋገጥ ሰውን በራሱ መልክ እና አምሳል ፈጥሮታል- ስለሆነም ሰው የማፍቀር፣ በማህበር የመኖር እና አንዳቸው ከሌላቸው ጋር የመዛመድ አቅም አላቸው፡፡

ስዚህ ነው እግዚአብሔር ሰው ስማህበር እና ስህብረት የፈጠረው:: የእግዚአብሔር "ስሉስ አሃድነት" እና በዚህ ውስጥ የሚገኘው ትምህርት ሁሉ በሰዎች መካከል ሊኖር ስሚገባ ህብረት ሞዴል የሚሆነው::

በመሆኑም ሰዎች ከሌላው ፍጥረት የተስዩ አቅምን ተጎናጽፈው በእግዚአብሔር ተፈጥረዋል::

1. **ስማፍቀር** ተፈጥረዋል:-

- እግዚአብሔር ን ስማፍቀር
- ባልንጀራቸውን ስማፍቀር

2. ሰዎች **በማህበር** ስመኖር/ስማህበራዊ ኑሮ/ ተፈጥረዋል:-

- ስሉስ አሃድ በሆነው በእግዚአብሔር ውስጥ ያስውን አንድነት በሞዴልነት ስማሳየት፤ ከሰዎች ሁሉ ጋር በፍቅር እና በእኩልነት መኖር::
- ማህበራዊ ኑሮ በፍቅር የተሳሰረ ህብረት ሙሉ ስሙሉ መገስጡን የምናይበት አውድ ነው::

3. ሰዎች **ስህብረት** ተፈጥረዋል:-

- ከፈጣሪያቸው ጋር
- ከተፈጠረው ዓስም ጋር:: ይህ በእግዚአብሔር የተሰጠ ህብረት ስተፈጠረው ዓስም እንክብካቤ ማድረግን እና መግዛትን/ማስተዳደርን/ እንደ ኃላፊነት የሚሰጥም ነው::
- ከሌሎች ሰዎች ጋር

4. ሰዎች ስራሳቸው ብቻ ሳይሆን ስሌሎች ሰዎች እና ስፍጥረታት እንክብካቤ ከማድረግ አቅም እና ኃላፊነት ጋር ተፈጥረዋል::

- እግዚአብሔር ፍጥረትን ወደመኖር ያመጣበት ምክንያት እና ትኩረት ከእርሱ ስተፈጠሩ ፍጥረታት፤ ከእርሱ ውጪ ስሆኑ ፍጥረታት ነው::

**ተግባር:-**

በእግዚአብሔር መልክ እና አምሳል መፈጠራችን ከሌሎች ጋር በሚኖረን ህብረት ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ ያሳድራል?

በኢየሱስ ክርስቶስ የተገስጠውን የእግዚአብሔር መልክ በመምሰል ባደግን ቁጥር፤ የእርሱን በማህበር የመኖር እና ፍቅር አቅምን በበስጠ እናንጸባርቃስን:: የእግዚአብሔር መልክ በአንድ ሰው አገልግሎት ውስጥ ሲገስጥ አገልግሎቱ ምን አይነት መልክ ይኖረዋል? (ከብዙ በጥቂቱ፤ አስቸጋሪ የሆኑ ሰዎችን የመታገስ አቅም፣ ወንድሞችን ወይንም እህቶችን ሳሳዘኑ ወገኖች ምህረት ማድረግ፣ እውነትን በፍቅር መናገር::)

## በተስግኦ ሲገስጥ

**ተግባር:-**

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን አምስት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንዲያነብቡ አምስት ሰዎችን ምረጥ፤ ዮሐ 3:16፤ ማቴ 20:28፤ ማር 10:45፤ ዮሐ 10:11፤ ፊሊ 2:5:11:: እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ተነብቦ እንዳበቃ

ተሳታፊዎች ከክፍሉ ስለተሰግዎ/የክርስቶስ በስጋ መገለጥ/ ምን እንደሚያስተምረን እንዲያብራሩ እድል ስጥ። በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ታላቅ ስለመሆን ምስጢር ባስተማረው ትምህርት ውስጥ ይህን እንዴት በተግባር አሳየ? እንዴት አድርገን ይህን ለማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ልንጠቀምበት እንችላለን?

እግዚአብሔር በሚታይ ቅርጽ ከሰዎች ጋር ለመኖር ስጋን ለበሰ መጣ። ከድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ፤ አማኑኤል እግዚአብሔር ከእኛጋር ነው። እርሱ እግዚአብሔር ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ወደ ዓለም የላከው ብቸኛ ልጁ ነው (ዮሐ 3፡16)። የመጣውም አብን ለእኛ ሊገልጥልን ነው። ምንም እንኳን ኢየሱስ በስጋ የተገለጠ አምላክ ቢሆንም፤ የመጣበት ምክንያት ደግሞ ለማገልገል እንጂ ለመገልገል፤ እንደውም ነፍሱን ለሰዎች አሳልፎ ለመስጠት እንደሆነ ነው የነገረን (ማቴ 20፡28፤ ማር 10፡45፤ ዮሐ 10፡ 11፤ ፊሊ 2፡5-10)።

በምስሉም እንደሰው በመገኘት ኢየሱስ እግዚአብሔር በእኛ በሰዎች ውስጥ ያስቀመጠውን እና ከእኛ የሚጠብቀውን የማፍቀር፣ የመዛመድ/ህብረት የማድረግ፣ ማህበረሰብ የመገንባት እና ለእግዚአብሔር መንግስት ጥቅም ይሆን ዘንድ ሌሎችን የማገልገል አቅም በተግባር አሳይቶናል። ይህንንም የከወነው ከደቀመዛሙርቱ ጋር በነበረው ህብረትና ከእነርሱ ጋር በመሆን በገነባው ማህበረሰብ ነው።ቅዱስ ማርቆስ በጻፈልን ወንጌል ኢየሱስ ይከተለው ከነበረ ብዙ ህዝብ አስራ ሁለቱን በመምረጥ "ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው" ይህንንም ያደረገው ለሁለት ጉዳዮች ነው። አንደኛው "ከእርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ" እና "ወንጌልን ለማድረስ ይልካቸው እና በአጋንንት እስራት ውስጥ ያሉትን ነጻ ያወጡ ዘንድ ነው።" (ማር 3፡14-15)። ከእርሱ ጋር ህብረት ለማድረግ የሚጠበቅብን ቅድመ ሁኔታ ምን እንደሆነ ተቀምጦልናል። ከእነርሱ ጋር የሚያሳልፈው ጊዜ ጥቂት እንደሆነ ስላወቀ፤ መልካሙ አረኛ አብዛኛውን ጊዜውን ያሳለፍ የነበረው አስራ ሁለቱን በማማከር እና በመደገፍ ነው፡- ያስተምራል፣ በተግባር ያሳያል እንዲሁም እርሱ ካረገ በኋላ የእርሱን ስራ ያስቀጥሉ ዘንድ ያስታጥቃቸዋል። በመጨረሻ ያስተላለፈላቸው መልዕክትም፤ እርሱ እነርሱን እንዳማከረ እና እንደደገፈ እነርሱም ሌሎችን እንዲያማክሩ እና እንዲደግፉ ነበር (ማቴ 28፡19-20፤ 20፡ 21)።

**"ማማከር እና ድጋፍን" መተርጎም**

በትምህርት እና በቢዝነስ ዘርፍ ማማከር እና ድጋፍ እንዲሁም በማማከር እና ድጋፍ ማገልገል አንድ አይነት መረዳት የሚፈጥሩ ናቸው። ምናልባት በዚህኛው ክፍል ጽንሰ ሀሳቡን መተርጎም ለምን አስፈለገ? ለዚህ ጥያቄ የሚከተሉት መልሶች ተቀምጠዋል፡-

1. ያልተዛባ ትርጓሜ ጽንሰ ሀሳቡን በተሻለ ለማጥራት እና ስለ ሂደቱ፣ በዚህ ውስጥ ስለሚሳተፉ ሰዎችና ስለሚኖራቸው ሚና በምናባችን የምንመስለው ትክክለኛ ስዕል እንዲኖረን ያደርጋል።

2. ዓላማውን በሚገባ ስንገልጥ፤ የተሳሳቱ ግምቶችን ወደ አዎንታዊ ጽንሰሐሳብነት መለወጥ ያስችለናል።

3. ትክክለኛ ትርጓሜ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት በየደረጃው የሚለካበትን እጥር ምጥን ያለ የብቃት መለኪያ እንዲኖረን ያደርጋል።

የሚከተለው የማማከር እና ድጋፍ ትርጓሜ ከግልጥ ወደ ውስብስብ/ከቀላል ወደ ከባድ የሚያመራ ነው። እያንዳንዱን በሚገባ ከተመለከትክ በኋላ፤ ሁሉም ጽንሰ ሐሳቦች ምን አይነት እንድምታ እዳላቸው ከግምት ውስጥ አስገባ። ተሳታፊዎችም በማማከር እና ድጋፍ ትርጓሜ ውስጥ ያስተዋሉትን እና ሲሰመርበት ይገባል ብለው ያመኑበትን ቁልፍ ሐሳብ ለቡድናቸው እንዲያካፍሉ አድርግ።

**ቀለል ያለ ትርጓሜ**

ቀለል ካለ ትርጓሜ ስንጀምር፡- ማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ሆን ብለን የምንጀምረው፣ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ **ህብረት** ሲሆን፤ አንድ ሰው **የሌላውን ሰው** አቅም እና ክህሎት ለማጎልበት **ልምዱን፣ ዕውቀቱን** እና **እይታውን/መረዳቱን** የሚያጋራበት መንገድ ነው።

ፖውል ስታንሊይ እና ሮበርት ጂ. ክሊንተን የተባሉ ጸሐፊያን ማማከር እና ድጋፍን እንደሚከተለው ገልጠውታል "አንድ ሰው ሌላውን ለማስታጠቅ እግዚአብሔር የሰጠውን ግብአት/የሚዳሰስ እና የማይዳሰስ ሃብት በማካፈል የሚመሰረት የህብረት ልምምድ ነው።" በማማከር እና ድጋፍ አማካይነት በሚፈጠር ህብረት ላይ ሌሎች አሳቦችን በማካተት ትርጓሜውን አስፍተውታል።

"ማመከር እና ድጋፍ የህብረት ሂደት ሲሆን አማካሪና ደጋፊው የሚያውቀውን ወይንም የተለማመደውን አንድ ነገር (ጥበብን፣ መረጃን፣ ልምድን፣ በራስ መተማመንን፣ ህብረትን፣ የኑሮ ደረጃን ወ.ዘ.ተ... የተመለከተ ግብአትን) በማማከር እና ድጋፍ የሚያገለግለው ሰው በሚሰጥበት ጉዳይ ይታጠቅ እና ይደረጅ ዘንድ በትክክለኛ ጊዜና ሁኔታ የሚያካፍልበት መንገድ ነው።"

**ተግባራት፡-**

- ተሳታፊዎች ያሰመሩበትን አሳብ እንዲያካፍሉ እድል ስጥ። ከዚያም ቁልፍ አሳብ ተብለው የሚቀርቡትን በሰሌዳ ወይንም በትልቅ ወረቀት ላይ አስፍር።
- ከተሳታፊዎች አንዱ ስለተመረጡ ቁልፍ ቃላት ትርጉም እንዲያብራራ ወይንም ምሳሌ እንዲሰጥ ጠይቅ። የሚከተሉትን ማንሳታቸውን እርግጠኛ መሆን ይገባሃል።

ቁልፍ ጽንሰ ሐሳቦች

(1) ማማከር እና ድጋፍ የህብረት ሂደት ነው (2) የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ የሚያካፍለው ልምድ አለው (3) አንድ ነገር ከአንዱ ወደ ሌላው ይተላለፋል (4) የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ እድገትን ያላልጣል እንዲሁም (5) የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ያስታጥቃል።

በቀጣይ ተሳታፊዎች ሁለተኛውን ትርጉም በማንበብ ከመጀመሪያው ትርጉም ጋር ያላቸውን አንድነት እና ልዩነት በማውጣት አዳዲስ አሳቦችን እንዲያሳዩ ጠይቅ። ይህ ትርጉም የተገኘው ጂም ኦስተርሃውስ እባ ጊሪ ተጀ *Masterful Mentoring* በሚል ርእስ ከጻፉት መጽሐፍ የተወሰደ ነው።

"ስሁሉም አይነት ዝንባሌ እና ዓላማ…ማማከር እና ድጋፍ አንድ ሰው በአንድ የሕይወት አቅጣጫ በክህሎት፣ ባህርይ እና ዕውቀት ያድግ ዘንድ የመርዳት ተግባር ነው። ይህ አሳብ በአብዛኛው ጥቅም ላይ ሲውል የሚችለው ከሁለት እንዳቸው የበለጠ ልምድና ዕውቀት ያለው ሲሆን በዚህም ከእርሱ በእድሜ የሚያንሰውን፣ አነስተኛ ልምድ ያለውን እና በዕውቀት ላዳበረው ሰው የሚያስተላልፈው አንድ ነገር ያለው ሆኖ ሲገኝ ነው። እነዚህን ጉዳዮች ከአንዱ ወደ ሌላው "የምናስተላልፍበት" መንገድ ማማከር እና ድጋፍ ይባላል (2012፡3)።"

ተግባር፡-

የተገቢነት ያለው ማማከር እና ድጋፍ ህብረትን የተለማመደ አንድ ፈቃደኛ ተሳታፊ፤ ያለፈበትን የማማከር እና ድጋፍ ሂደት ከላይ በጠቀስናቸው ጸሐፊያን ከተሰጡት ትርጓሜዎች ጋር በማነጻጸር እንዲያቀርቡ እድል ስጥ። ጠቅላላውም ተሳታፊ ትርጓሜዎቹን እንዲያወዳድሩ ጊዜ ስጥ።

የውይይቱን ትኩረት በአንድ ጉዳይ ላይ ለማድረግ እና አቅጣጫ ለማስያዝ እነዚህ ጥያቄዎች ያስፈልጉህ ይሆናል፡-

- የትርጓሜዎቹ ተመሳሳይነት ምንድን ነው?
- ምን አይነት አሳቦችን ይጋራሉ?
- ሁለተኛው ትርጓሜ ምን አይነት አሳቦችን በተጨማሪነት ያቀርባል?

## "በማማከር እና ድጋፍ የሚገለገልን ሰልጣኝ" መተርጎም

ከ1978 እ.ኤ.አ በፊት በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ውስጥ ሁለተኛውን ወይንም ተገልጋዩን/ተመሪውን ለመግለጥ የቀረቡት ቃላት የተግባር ሰልጣኝ የሚለው ሲሆን ይህም አንድ ሰው ክህሎቱን ከፍ ለማድረግ በአንድ መስሪያ ቤት ውስጥ የሚወስደው የተግባር ስልጠና ሲሆን ይህ ቃል ከፍ ያለ ጥገኝነትን ስለሚያንጸባርቁ በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለን የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ለመወከል የሚሆን ጥልቀት ስለሌለው "በማማከር እና ድጋፍ የሚገለገል ሰልጣኝ" የሚለውን ቃል ተቀባይነት ያለው ነው በማለት መርጠናል። በልምድ የዳበረ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት የሚለው ክፍል ላይ የሚገኘውን ትርጓሜ በማጤን ተሳታፊዎች በማማከር እና ድጋፍ ስር ስላለ ሰልጣኝ ባህርይ ተሳታፊዎች በበለጠ እንዲረዱ ከዚህ በታች የቀረቡትን ቁልፍ ቃላት/ሐረጎች ተጠቀም።

በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ ጎልማሳ/አዋቂ ተማሪ ነው። እንደ ጎልማሳ/አዋቂ ተማሪነቱ፤ በአንድ ፋብሪካ ውስጥ የተግባር ልምምድ ከሚወስድ ወይንም በአንድ ግለሰብ ጥበቃ ስር ካለ እና ሁሉን ነገር ሰርተው ከሚያቀርቡለት/ፈትተው ከሚያጎርሱት/

ሰልጣኝ በተቃራኒ የሚወጣው አንድ ተስዶች የሚታወቅ ሚና አለው። "በመሆኑም ውጤታማ የሆነ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት የሚመራው በአሰልጣኙ ሳይሆን በሰልጣኙ ነው።" በሌላ አነጋገር በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ የሚለው መገለጫ ራሱ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎትን እና በዚህ ውስጥ ያለን ህብረት በተለየ መንገድ የምንመለከትበትን እንድምታ ያሳየናል። በማማከር እና ድጋፍ ስር የሚሰለጥነው ተማሪ በዚህ ተግባር ላይ ተከታይ ሳይሆን ንቁ ተሳታፊ ነው። በማማከር እናድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ "የሚሰጠውን ዕውቀት፣ ክህሎት፣ እይታ፣ አመለካከት ወይንም ጥበብ ለመፈተሽ፣ ከራሱ ጋር ለማዋሃድ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚችለውን ያህል ጥረት የሚያደርግ ነው...እንዲህ ያለውን መረዳት፣ አመለካከት ወይንም ጥበብ የሚፈልገው በተገቢው ጊዜና ቦታ እድገትን እና መልማትን በሚያፋጥን ሁኔታ ለመጠቀም ነው።" በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ተማሪ የሆነ ግለሰብ ማንነት ሙሉ ለሙሉ በመሸከም የሌላኛው ሰው ሁለንተና ተሸካሚ አይደለም፤ ከዚህ ይልቅ የራሱን ስብዕና እና የተለየ ማንነት በመገንባት ሂደት ውስጥ የሌሎችን እርዳታ እያገኘ ያለ ግለሰብ ነው።

1. በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ እንደ ጎልማሳ ተማሪነቱ ለአገልግሎቱ መዳበር የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ምልከታ፣ ክህሎት እና ዕውቀት ለይቶ ያውቃል።

2. በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ "ጎልማሳ ተማሪ እንደመሆኑ በማስተዋል የሆነ የእድገት ጉዞን ያደርጋል።"

3. በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ተማሪ በስልጠናው ውስጥ ተከታይ ከመሆን ይልቅ ንቁ ተሳታፊ ነው።

4. በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ የሚሰጠውን ዕውቀት፣ ክህሎት፣ እይታ፣ አመለካከት ወይም ጥበብ ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ይችል ዘንድ ለመገምገም፣ ከራሱ ጋር ለማዋሃድ እና ለመጠቀም የሚችለውን ያህል ጥረት ያደርጋል።

5. በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ እንደየአስፈላጊነቱ እርዳታ ይጠይቃል በተሰጠውም ጊዜ አገልግሎቱን ማጎልበትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በአግባቡ ይጠቀምበታል።

6. በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ በልዩነት የሚታወቅበትን ማንነት ያዳብር ዘንድ ድጋፍ የሚደረግለት ግለሰብ ነው።

7. ውጤታማ የሆነ የማማከር እና ድጋፍ ህብረት ውጤታማ የሚሆነው ከአሰልጣኙ ይልቅ በማማከር እና ድጋፍ ስር ባለው ሰልጣኝ ሲመራ ነው።

**ተግባር:-**

ተሳታፊዎችን በቡድን መድብ፤ ከዚያም ከ Osterhouse and Teja ያገኘሽውን በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለን ሰልጣኝ ትርጓሜ ሁሉም እንዲያነብቡት በማድረግ፤ በዚህ ንባብ ውስጥ ያገኙት አሳብ ማማከር እና ድጋፍ

አገልግሎትን በተመለከተ የነበራቸውን አመለካከት እንዴት እንደተቀየረ በሚከተሉት ጥያቄዎች መሰረት እንዲወያዩ አድርግ፡-

- በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለን ተማሪ ባህርይ ለመግለጥ ከላይ የተዘረዘሩትን በራስህ መስፈርት መሰረት እንደገና ዝርዝራቸውን አስፍር፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በሚገባ እንዲዘረዘሩ የምትፈልጋቸው ባህርያት አሉ?
- በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት የሚመሰረተው ህብረት የሚመራው በማማከር እና ድጋፍ ስር ባለው ሰልጣኝ ከሆነ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ሚና ምንድን ነው?

**ደቀመዝሙር፣ አማካሪ እና ደጋፊ፣ አሰልጣኝ**

እዚህ ነጥብ ላይ በአብዛኛው በታወቁ ውይይቶች ስለማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት የሚፈጠረውን ብዥታ ማጥራት አስፈላጊ ነው፡፡ ኢየሱስ በምድረ አገልግሎቱ ማብቂያ ላይ ደቀመዛሙርቱ ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱና አህዛብን ሁሉ ደቀመዝሙር እንዲያደርጉ አዝዟቸው ነበር፡፡ ደቀመዝሙር ማድረግ እና የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት አንድ አይነት ትርጉም እና አንድ አይነት ግብ አላቸው? ደቀመዝሙር ማድረግን እንዳንድ ጸሐፊያን እንደ ዕድሜ ዘመን ስልጠና ሲወስዱት፤ ሌሎች ደግሞ የክርስትና ኑሮ የመጀመሪያ ስልጠና አድርገው ይወስዱታል፡፡ በምን መልኩ ደቀመዝሙር ማድረግ ለማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት መንገድ ይከፍታል? የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ደቀመዝሙር ከማድረግ እና ከማሰልጠን በጽንሰ አሳብ ደረጃ እንዴት ይለያል?

**ተግባር፡-** ከድረ ገጻችን ላይ መጽሐፉን ካወረዳችሁ በመገቢያው ላይ ከምታገኙት በልምድ የዳበረ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት በሚለው ርዕስ ስር ከላይ ባነሳናቸው ጽንሰ አሳቦች መካከል ያለውን ልዩነት ተመልከቱ፡፡ ተሳታፊዎች በእነዚህ ጽንሰ አሳቦች ዙሪያ በመወያየት በመካከላቸው ያለውን ልዩነት እንዲረዱ እና በእያንዳንዱ ደረጃ የሚገኝ የመሪነት ስልጠና ምን መሆን እንደሚገባው እንዲለዩ አድርግ፡፡ ከዚያም ለሶስቱም ምን አይነት ስልጠና ሲሰጥ እንደሚገባ ተሳታፊዎች ምሳሌ እንዲሰጡ አድርግ፡፡

# የትምህርት አቀባበል ዘዴ

**የድምጽ ወይንም የቃል ተማሪዎች** እንዲሁ በንግግር የሚሰጥን መረጃ በመቀበል ልዕቀትን ማምጣት ይችላሉ፡፡ እንዲህ ባለው የመማር ዘዴ ተፈጥሮአቸው የሆነ ተማሪዎች በክፍልውስጥ በቃል የሚሰጥን ትምህርትና ውይይትን ማስታወስ እና ያንን ዕውቀት ለዘለቄታው ማኖር ይችላሉ፡፡

**የእይታ ተማሪዎች** ሲሰጥ የታሰበው መረጃ ሲነበብ ወይንም በስዕላዊ መልክ ሲታይ ከምንም በላይ ያንን መረጃ የማወቅ እና የማስታወስ አቅማቸው ይጨምራል፡፡ ለማስታወስ ስዕላዊ መግለጫዎችን፣ ግራፎችን እና ሰንጠረዥ የሚጠቀሙ

ማስረጃዎችን ማዕከል አድርገው ይጠቀማሉ፡፡

**የተግባር ተማሪዎች (ነገሮችን በመነካካት የሚማሩ)** ወይንም ከቁስ,ጋር መስተጋብር ያላቸው ተማሪዎች ልንላቸው እንችላለን፡፡ እነዚህ ተማሪዎችን ግኝት ፈላጊ ሲሆኑ የመማር አቅማቸው ከፍ የሚለው ነገሮችን በመንካት እና በመመራመር ነው፡፡

**አካባቢን መሰረት አድርገው የሚማሩ ምቹ** አካባቢ የመማሪያ አካባቢ ምቹ መሆን፣ በቂ ብርሃን መኖር እና ተገቢ የሆነ የሙቀት መጠን ያለበት ቦታ መማር ከባቢያዊ ተማሪዎችን የመማር አቅማቸው ከፍ እንዲል ማድረግ ብቻ ሳይሆን የተቀበሉትን መረጃ ከማንነታቸው ጋር ለማዋሃድ ብሎም ትምህርቱን ለዘለቄታው ለማኖር ይረዳል፡፡

## የጎልማሶችን ትምህርት የተመለከተ መሰረታዊ መሳምት

የጎልማሶች ትምህርት አሳብ የመነጨው ከማልኮም ኖውልስ እና ባልደረቦቹ ካደረጉት ጥናት እንደሆነ ለተሳታፊዎች አብራሩ፡፡ የጎልማሳ ትምህርት መርሃ ግብራቸው መሰረት ያደረገው ከታች በቀረቡት እና በእርግጠኝነት ለአዋቂዎች ትምህርት አቀራረብ መሰረት ይሆናሉ ባሏቸው አራት መሳምቶች ላይ ነው፤ እነርሱም፡-

1. ሰዎች ወደ ብስለት ሲደርሱ፤ ምርጫ በማድረግ አቅማቸው ልክ ለውጥን ይለማመዳሉ፡፡ ጨቅላነት እና ታዳጊነት የሚታወቅበት እንዱ ጉዳይ ፍጹም በሆነ ጥገኝነት ነው፡፡ መብሰል የሚያተርፍልን ራስን መቻል እና ራስን የመምራት ብቃት ነው፡፡ አዋቂዎች ለመረጡት ምርጫ ኃላፊነት ይወስዳሉ፡፡ ይሄኔ ነው አንድ ሰው በስነልቦናው አዋቂነት ደረጃ ላይ ደርሷል የምንለው፡፡

2. ወደ ጎልማሳነት የምንሸጋገርበት ሂደት በራሱ የተለያዩ አዳዲስ ልምዶች ያቀርበናል፡ ፡ ዓዋቂ ተማሪዎች ከሕይወት ተሞክሮአቸው ያገኙትን ልምድ ወደ መማር ማስተማር ሂደቱ ማምጣታቸው ሲማሩ ካሉት አዲስ ትምህርት ጋር የማዛመድ ከፍተኛ ብቃት ስላላቸው ተጠቃሚነታቸውም በዚያው ልክ ይጨምራል፡፡ ይህ ልምዳቸውን ያጠራቀሙበት የሕይወት "ባንክ" ለአዋቂዎች ትምህርት መተኪያ የሌለው ውድ ነገር ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተለመደው የትምህርት አሰጣጥ ስልት ያካበትነውን ልምድ በተግባር የምንገልጥበትን መንገድ ማለትም ልምድን መሰረት ያደረገ ትምህርት፣ ተግባቦት እና በተማሪው የሚደረግ ልምድን የመተንተን ሂደት በመጠቀም የተማሪውን ተሳትፎ በበለጠ ያዳብረዋል፡፡ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ የትምህርት አሰጣጡ ከአንድ አቅጣጫ (ማለትም ከአስተማሪ ወደ ተማሪ ብቻ) መሆኑ ይቀርና ባለሁለት አቅጣጫ (ማለትም ከአስተማሪው ወደ ተማሪው እና ከተማሪው ወደ አስተማሪው) ይሆናል፡፡

3. አንድ ሰው ወደ ብስለት ሲደርስ በቀለም ትምህርት የተሻለ ውጤት ለማምጣት እና ልቀ ለመገኘት የሚያደርገውን ጥረት አዲስ ክህሎት እና

አቅም ለማዳበር ቢደረግ ጥረት ይተካዋል፡፡ እነዚህ ፍላጎቶች ደግሞ የሚወለዱት ማበረሰቡ የሚሰጠውን ኃላፊነት በላቀ ደረጃ ለመወጣት ከሚመነጭ ፍላጎት ነው፡፡ በመሆኑን አዲሱ ትምህርት ከሚፈለገው ተግባር ተኮር የዕውቀት ልማት ጋር አብሮ የሚሄድ ሲሆን ይገባዋል፡፡

4. የተለመደው የትምህርት አሰጣጥ የትምህር ዘርፍ ተኮር ነው፡፡ አስተማሪው ለተማሪው ለወደፊት ሕይወቱ ይጠቅማል ብሎ ያሰበውን የትምህርት ዘርፍ/ኮርስ/ ያዝለታል፡፡ አዋቂዎች ወደ ትምህርት የሚገቡት በሕይወታቸው ብቁ ሆነው ለመገኘት እና የጎደላቸውን ክሂል ለመሙላት ነው፡፡ ትምህርቱን የሚፈልጉበት እሳቤ የተገኘው ችግር ተኮር ወይንም ሕይወት ተኮር ከሆነ ልምድ ነው፡፡ በአዋቂዎች ትምህርት ውስጥ አንድ ልብ የምንለው ጉዳይ የትምህርት አሁናዊነትን ነው፤ አዋቂ ተማሪዎች ዛሬ የተማሩትን ነገ መተግበር ፈልጋሉ እንጂ ለረቅ ጊዜ ለመጠቀም አይደለም፡፡

## አዋቂ ተማሪዎችን በማማከር እና ድጋፍ የማገልገል ጥቅም

ከዚህ በታች ሰባት መሰረታዊ የመርህ መላምቶች ተዘርዝረዋል፡፡ እያንዳንዱ መርህ በማማከር እና ድጋፍ ስለምናገለግለው ሰልጣኝ መገለጫ ተሳታፊዎች እንዲያውቁና የትምህርት ሂደቱን በተሻለ የተሳለጠ ለማድረግ ሚናቸውን እንዲወጡ ያስችላቸዋል፡፡

**የመጀመሪያ መርህ፡-** **ጎልማሳ ተማሪ ለምን የሚለውን ማወቅ ይፈልጋል፡፡**

ዓለም ተለዋዋጭ እንደመሆኗ በማማከር እና ድጋፍ ለምናገለግለው ሰልጣኝ አዲስ ዕውቀት መስጠት ተጨማሪ ትምህርት ይፈልጋል፡፡ ጎልማሶች በእድሜ እንደመብሰላቸው ካላቸው የተጣበበ ጊዜአቸው ቀንሰው አንድ ትምህርት ከመማራቸው ወይንም ትምህርት ቤት ከመግባታቸው በፊት ለምን እማራለሁ የሚለውን ማወቅ ፈልጋሉ፡፡

**ጥቅም፡-** በማማከር እና ድጋፍ ስር የሚሰጥነው ተማሪ የሚካፈለውን ልምድ ጥቅም ምን እንደሆነ ተረድቶ ይህን አገልግሎት ይጀምራል፡፡

**ተግባር፡-** ከተሳታፊዎች መካከል ምንያህሉ "በዚህ ስልጠና ለምን መሳተፍ ፈለጉ" ብለው ራሳቸውን እንደጠየቁ እንዲናገሩ እድል ስጥ፡፡ ይህን ጥያቄ መመለሳቸው ለመማር ማስተማር ሂደቱ ምን አይነት ጥቅም ይሰጣል? እንዴትስ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎቱን ያሳልጣል?

ተሳታፊዎች በማማከር እና ድጋፍ ከሚያገለግሉት ተማሪ ጋር አብረው በሚሰሩበት ወቅት ተማሪው ቤተክርስቲያን የመትከል አቅም ማዳበር ለምን እንደሚጠቅም ማወቅ ይኖርበታል፡፡ የአገልጋዩ እና ተገልጋዩ የውስጥ ዝንባሌ ምን መሆን አለበት?

**ሁለተኛ መርህ፡- ጎልማሳ ተማሪዎች እራሳቸው ለራሳቸው ኃላፊነት የሚወስዱ እና ራሳቸውን የሚመሩ ናቸው፡፡**

ጎልማሶች ራሳቸውን እንደሚመሩ ያምናሉ። በማማከር እና ድጋፍ የምናገለግላቸው ጎልማሶች ለሚወስኑት ውሳኔዎች በሙሉ ኃላፊነት እንደሚወስዱ እና የራሳቸውን ሕይወት በራሳቸው እንደሚመሩ የተረዱ ናቸው። ይህም ማለት በዚህ ስልጣኝ ላይ የእኛን አሳብ ለመጫን መሞከር ትርፉ ተቃውሞ ብቻ ነው። ጎልማሳ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ውስጥ እንደ ጓደኛ እንዲታዩ እና ልምድ እንዳለው ግለሰብ መከበርን ይፈልጋሉ።

**ጥቅም፡-** በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለው ሰልጣኝ በዚህ ጊዜ ያስፈልገኛል ለሚለው ዕውቀት ለማግኘት ይበጀኛል የሚለውን የትምህርት ዘርፍ ለመረጠ። ይህ ደግሞ የሚያሳየን በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ውስጥ ሰልጣኝ እና አሰልጣኝ ያላቸው ህበረት፤ አንዱ የበለጠ ዕውቀትና ልምድ ኖሮት ሌላውን በማስታጠቅ እና በመምራት፤ እንደ አብሮ ሰራተኛ በጋራ ያስቀመጡት ውጤት ላይ ለመድረስ ይሰራሉ፤ ይህም ማለት አንድ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ የተሻለ ልምድ ካለው አነስተኛ ልምድ ያለውን ይመራል ማለት ነው።

**ተግባር፡-** ይህ አዎንታዊ ምርጫ በማማከር እና ድጋፍ ልምምዶችን ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ እንደሚኖረው ተሳታፊዎች እንዲያመለክቱ ጠይቅ። የሚመልሱትን መልስ ከሰማህ በኋላ፤ እንዴት ነው የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች የተገልጋዩን የግል ኃላፊነት እና ራስን የመምራት መብቱን ሳይነካ ተገልጋዩ የሚያስፈልገውን ዕውቀት እና ክህሎት ማግኘቱን የሚያረጋግጠው? በዚህ በጎልማሶች የትምህርት ባህርያት ውስጥ አሉታዊ የሆኑ ጉዳዮች አሉ? ካሉ እንዴት ነው ልንይዛቸው የሚገባን?

በማማከር እና ድጋፍ የሚያገለግሉ አገልጋዮች በእነርሱ ስር የሚሰለጥኑ ሰዎች ምን መማር እንደሚፈልጉ፣ ምን አይነት ክህሎት ማዳበር እንሚፈልጉ እና የትኞቹን የማንነት መገለጫ ባህርያት በበለጠ ማዳበር እንዳለባቸው እንደሚያስቡ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ተማሪ የሚፈልገውን ይመርጥ ዘንድ ዝርዝር መርሃ ግብሮችን ማቅረብ አገልግሎቱን ለማሳደግ እገዛ ያደርጋል።

**ሶስተኛ መርህ፡- ጎልማሳ ተማሪዎች የተጠራቀመ ልምድ ባለቤት ናቸው**

የተማሪው ልምድ ለመማር ማስተማሩ ሂደት መሳለጥ የሚረዳ የካበተ ሃብት ነው። ጎልማሶች ወደ ትምህርት ከባቢ የሚመጡት ከልጆች በተለየ ከፍ ባለ ዕውቀት እና ከሌሎች የሚለዩበትን ልምድ ይዘው ነው።

**ጥቅም፡-** የጎልማሶች ልምድ አሁን ሳሉበት ሁኔታ ሊጠቀሙበት የሚያስችል ዕውቀት መሰረት ሊሆናቸው ይችላል። በሕይወት ዘመን የተጠራቀመ ልምድ ጎልማሳ ተማሪዎች አዳዲስ ዕውቀቶችን እንዲማሩ እና ካላቸው ቅድመ ዕውቀት ጋር እንዲያስማሙ ያስችላቸዋል። ስለሆነም በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለው ተማሪ

ልምድ በሕይወቱ ለውጥን ለማምጣት እንደመሸጋገሪያ ልንወስደው እንችላለን፡፡

**ተግባር፡-** አንድ ወይንም ሁለት ተሳታፊዎችን በመምረጥ ከአገልግሎት ውጪ በነበረበት ወቅት የነበራቸው ልምድ እንዴት በአገልግሎት ውስጥ የሚገጥማቸውን ችግር ለመፍታት ወይንም በአገልግሎት አብረዋቸው ከሚሆኑ ሰዎች ጋር የሚቀራረቡበትን መንገድ እንዲቀይሩ እንደረዳቸው እንዲናገሩ እድል ስጥ፡፡

በማማከር እና ድጋፍ ስር ላለ ሰልጣኝ ስለቀደመ ሕይወት (ስኬትም ይሁን ውድቀት) ማካፈል ከዚህ ልምድ እንዲማር፣ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን እንዲሁም ሌሎችም በዚህ ታሪክ ይባረኩ እና ይማሩ ዘንድ እንዲጸልይ ይረዳዋል፡፡

**አራተኛ መርህ፡- ጎልማሳ ተማሪዎች ችግር ተኮር ናቸው**

ጎልማሶች ከዚህ ቀደም ባላቸው ልምድ መፍታት የማይችሉት አዲስ ችግር ሲገጥማቸው፤ ትኩረታቸው ሁሉ ይህን አዲስ ችግር መፍታት በሚያስችሏቸው አዳዲስ መንገዶች ላይ ይሆናል፡፡ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎቱን በእኛ ስር እየሰለጠነ የሚገኘውን ተማሪ የገጠመውን ችግር በመፍታት ዙሪያ ካደረግን የሚገኘው ውጤት ከፍ ያለ ይሆናል፡፡

**ጥቅም፡-** በአገልግሎት ውስጥ የሚገጥሙ ችግሮች እና በዚህ ውስጥ የሚገኙ ልምዶች የሰልጠናውን ትኩረት አቅጣጫ ይወስናሉ፡፡ በማማከር እና ድጋፍ ስር ያሉ ሰልጣኞች ለገጠማቸው ችግር ተጨባጭ የሆነ መፍትሄን እንጂ ሳሉበት ጉዳይ የተለያዩ ቀመሮችን እያነሳን ይህ ይሰራል ይህ አይሰራም የሚለውን መፈተሽ አይደለም፡፡

**ተግባር፡-** ተሳታፊዎች በእነርሱ ማማከር እና ድጋፍ ስር ላለ ሰልጣኝ ችግር ይሆናል ብለው ያካፈሉት ልምድ፤ በእርግጥ ችግሩን በተጨባጭ ለመፍታት ያስቻለበትን ሁኔታ እንዲናገሩ እድል ስጥ፡፡

**አምስተኛ መርህ፡- የጎልማሶች ትምህርት ሕይወት ተኮር ነው**

ጎልማሶች ለመማር ዝግጁ የሚያደርጋቸው ለአንድ ጉዳይ መፍትሄ ለማምጣት ለሚፈልጉት ጉዳይ ዝግጁ አስመሆናቸውን የሚያውቁበት አጋጣሚ ነው፡፡ ይህም አዳዲስ ክህሎቶችን በመማር የገጠማቸውን ችግር የሚፈቱበትን አቅም ለማዳበር ወደትምህርት የሚያቀርባቸው ገፊ ምክንያት ነው፡፡

**ጥቅም፡-** በማማከር እና ድጋፍ ስር የሚሆኑ ተማሪዎች ወደ ማማከር እና ድጋፍ ህብረት የሚገቡት ቀድመው ለለዩት ችግር መፍትሄ ለማግኘት ነው፡፡

**ተግባር፡-** በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ ትምህርት የሚፈልገው ለአገልግሎት እና በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስፈልገው እና የሚረዳው አዳዲስ ክህሎትና ብቃት በማዳበር በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ለመጠቀም ነው፡፡ ይህ እንዴት የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎትን እንደሚያሳልጥ ተሳታፊዎችን ጠይቅ፡፡

**ስድስተኛ መርህ፡- የጎልማሶች ትምህርት ሕይወት ተኮር ነው**

በማማከር እና ድጋፍ ስር ላለ ሰልጣኝ ትምህርት የብቃት ደረጃቸውን ከፍ የሚያደርግ እና ሙሉ አቅማቸውን መጠቀም የሚያስችላቸው ሂደት ነው፡፡ የዚህ የትምህርት ስርአት ከተለመደው እና ትምህርትን ማዕከል ካደረገ ስርአት ጋር በተወሰነ መልኩ የሚቃረን ነው፡፡

**ጥቅም፡-** ሰልጣኞቻችን ጎልማሳ ተማሪዎች እንደመሆናቸው የትምህርት ምልከታቸው ግዳጅ ተኮር ወይንም ችግር ተኮር ሲሆኑ፣ አሁን ላሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ምላሽ ይፈልጋሉ፡፡ ሁልጊዜም አንገብጋቢ ምላሽ የሚያሻው ጥያቄ ያላቸው ይመስላል፣ ዛሬ የሚማሩት ሁሉ አሁን ላሉበት ሁኔታ ለመጠቀም ይፈልጋሉ፡፡

**ተግባር፡-** አንድ ወይንም ሁለት ተሳታፊዎች፣ ከላይ ያነሳነውን መርህ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎታቸውን በምን መልኩ እንዳስተካከለው አሳባቸውን እንዲያካፍሉ ጊዜ ስጣቸው፡፡

**ሰባተኛ መርህ፡- ጎልማሳ ተማሪዎች ራሳቸውን ለትምህርት የሚያነሳሱ ናቸው**

ይህም ማለት ጎልማሳ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት የሚገፋቸው ከውጫዊ ምክንያት ይልቅ ውስጣዊ ምክንያት ነው፡፡ ትምህርትም ጥቅሙ የሚሰካው ለውስጥ ማንነታቸው በሚሰጠው በራስ መተማመን፣ የኑሮ ደረጃ፣ የሙያ እርካታ እና/ወይንም የመፈጸም አቅምን ለማሳደግ በሚሰጠው ጥቅም ነው፡፡

**ጥቅም፡-** በማማከር እና ድጋፍ የሚሰጥኑ ተማሪዎች ምናልባት ለውጫዊ የመማር ግፊት ምላሽ ይሰጡ ይሆናል፣ ነገር ግን ለመማር የሚቀሰቅሳቸው ወሳኝ ጉዳይ ያስቀመጡትን ግብ ለመምታት የሚያግዛቸው የውስጥ ግፊት ነው፡፡ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ሰልጣኞቹን ለትምህርት ማነሳሳት አይጠበቅበትም፡፡

የሰባቱ መርህ ማጠቃለያ

ይህን ስልጠና በምትሰጥበት ወቅት፣ እያንዳንዱ መርህ በማማከር እና ድጋፍ ስር እየሰለጠነ ስላለው ተማሪ የሚያስተምረንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቅርብ፡- (1) እንዴት ይህ መረጃ ስለማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ሂደት መረጃ የሚያቀርብልን? (2) እንዴት ነው ተሳታፊዎች ይህን መረጃ በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት አቀራረባቸው ጋር አስማምተው የሚጠቀሙበት?

**ተግባር፡-** በዚህ ስልጠና ተሳታፊዎች ስለጎልማሶች ትምህርት ያገኙት አዲስ ዕውቀት በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት አቀራረባቸው ላይ ምን አይነት ለውጥ እንደሚያመጣ ጠይቃቸው፡፡ እያንዳንዱ ተሳታፊ ከቀረቡት ሰባት መርሆች ውስጥ ከሚያገለግለው ሰልጣኝ ጋር በሚኖረው ህብረት ሁሉ ከልቡ ሊያኖረው የሚወደው አንድ መርህ ምን እንደሆነ እንዲገልጥ እድል ስጥ፡፡

## መልካም የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ መገለጫዎች

**ተግባር፡-**

ይህን ክፍለ ትምህርት ተሳታፊዎች ከዚህ ቀደም በግለሰቦች የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ስር የነበራበትን ዘመን እንዲያስቡ በመጠየቅ ጀምር፡፡ ያግለሰብ መልካም የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ነበር? ከሆነ፤ ይህን ግለሰብ መልካም የማማር እና ድጋፍ አገልጋይ ያደረገው ምንድን ነው? መልካም አማካሪ እና ደጋፊ መገለጫዎች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

መልካም የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ትኩረታችንን የሚስቡ በርካታ መገለጫዎች አሉት፡፡ እናንተም ከመገለጫዎቹ ጥቂቶቹን እንደገመገማችሁት፣ ተሳታፊዎችም የግል አስተያየታቸውን ማለትም በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎታቸው ውስጥ እነዚህ አስፈላጊ መገለጫዎች መታየት አስመታየታቸውን ለሌሎች በማሳየት ተሳተፉዋል፡፡

## 1. መልካም የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ጥሩ አድማጭ ነው

እንዲህ የሚል የስፓኒሾች ምሳሌአዊ ንግግር አለ "ሁለት ጆሮ እና አንድ አፍ ኖሮን የተፈጠርነው የምንናገረውን እጥፍ እንድንሰማ ነው፡፡ ስለሆነም የምንናገረውን እጥፍ መስማት ይገባናል፡፡" ጥሩ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ብዙ ከማውራት ብዙ መስማትን መርጣሉ፡፡ የሚናገሩትም በእነርሱ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ስር ያለውን ሰልጣኝ ጥያቄ ለመጠየቅ እና ለመስማት ነው፡፡

አንዳንዶች እንዲህ ያለውን ማድመጥ አረጋጋጭ ማድመጥ ሲሉት ሌሎች ደግሞ ንቁ አድማጭነት ብለው ያቀርቡታል፡፡ በሁለቱም አባባል ውስጥ ያሉት ገላጭ ቃላቶች ተሳትፎን አመላካች ናቸው፡፡ እንዲህ ያለው ማድመጥ ዳተኛ ከሆነ ማድመጥ ማለትም ከአንድ ሰው ጋር በምናወራበት ወቅት ከልብ ከማድመጥ ይልቅ ከእኛ ጋር ለሚያወራው ሰው በቀጣይ ምን እንደምንመልስለት እያሰብን ማድመጥ ነው፡፡ አረጋጋጭ ወይንም ንቁ አድማጭ ስንሆን ሌሎች ለሚናገሩት ነገር ጠለቅ ያለ ትኩረት ይኖረናል፡፡ ተናጋሪው የሚያሳየውን የሰውነት እንቅስቃሴ ሳይቀር የሚያስተላልፈውን ቃላት አልባ ንግግር ሳይቀር በሚገባ በማጤን ተናጋሪው ምን እንደሚል መስማት ብቻ ሳይሆን ምን ለማለት እንደፈለገ ለማወቅ እንጥራለን፡፡ አንድ የማማከር እና ድጋፍ ከፍተኛ አገልጋይ ይህን የማድመጥ አይነት እንዲህ ገልጦታል "የተማሪውን ዓለም ከውስጥ ገብተን ለማሰስ የምንሞክርበት ንቁ መስተጋብር ነው፡፡"

**ተግባር፡-**

1. ከተሰታፊዎች ውስጥ ፈቃደኛ የሆነ ሰው በመውሰድ ዳተኛ የሆነውን አሰማም በሞዴል መልክ አቅርብላቸው፡፡ ይህን ለማሳየት አንድ ሰው በሳምንቱ ውስጥ ስላሳለፈው ሲናገር ከሃሳቡ ጋር የማይገናኝ አሳብ በማንሳት እና ትኩረት ባለመስጠት

አንተ በሳምንቱ ውስጥ ስላሰለፍከው ማውራት ነው፡፡ በቀጣይ ደግሞ ስለ ንቁ የማድመጥ ሂደት ሞዴል የሚሆን ንግግርን ከፈቃደኛ ተሳታፊው ጋር አድርግ፤ በዚህ ጊዜ ተሳታፊው ዛሬ እና ነገ ሊያደርገው ስለሚፈልገው ጉዳይ ሲያወራ የሚያወራውን ነገር በሚገባ ስመረዳት የሚያግዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ እንዴት አድርገው ያሰቡትን ጉዳይ እንደሚመለከቱት ለማረጋገጥ በመሞከር ወይንም ስለጉዳዩ ምን እንደሚሰማቸው በመጠየቅ ማሳየት፡፡ ትኩረትህን ሁሉ ተሳታፊው ሲያወራ የሚፈልገውን ስመረዳት አድርግ፡፡

2. ተሳታፊዎች ሳለባቸው ችግር የራሳቸውን ችግር ፈቺ እቅድ ከማምጣት ይልቅ፤ የገጠማቸውን ጉዳይ ለሌላ ሰው በቃላቸው በማነብነብ የማድመጥን ስርአት በሚጥስ ሁኔታውስጥ ተገኝተው ያውቁ እንደሆን ጠይቅ፡፡ ተሳታፊዎች እንዲህ ያለ ገጠመኝ ኖሯቸው ያውቅ እንደሆን ከአጠገባቸው ላሉ ሁለት ወይንም ሶስት ሰዎች እንዲነግሩ እድል ስጥ፡፡ ለዚህ ተግባር የሚሆን በቂ ጊዜ ስጥ፡፡

ጥሩ አድማጭነታችን ነገሮችን በእኛ ስር ከሚሰለጥነው ግለሰብ ካለበት ሁኔታ እንጻር እንድናስብ ከማድረጉም በላይ ሰልጣኞችንም አሳቡን በሚናገርበት እና መፍትሄ ይሆናሉ የሚላቸውን መንገዶች በሚጠቁምበት እና ያስፋበትን መንገድ በሚገመግምበት ሂደት ችግር ፈቺ የመሆን አቅሙን እንደሚጨምር አብራርተህ ለተሳታፊዎች አሳውቅ፡፡ አገልጋዩ ከማድመጥ ይልቅ መናገር ላይ ትኩረት የሚያደርግ ከሆነ ከላይ ያኖራቸዋል ብሎን ያስቀመጥነው የችግር ፈቺነት ብቃትን አያዳብረም፡፡ የራስን ችግር በራስ አቅም መፍታት ሌሎች ሁሉን ጥንቀቀ አድርገው ከሚያቀርቡልን ያለምንም ጥርጥር የተሻለ ነው፡፡

**2. መልካም አማካሪ በሕይወት ውስጥ በሚፈጠር " የአሁን ጊዜ" ላይ በትኩረት ይወያያል፡፡**

በማማከር እና ድጋፍ አማካይነት የሚፈጠር ህብረት ሰልጣኙ እየተጋፈጠ ያለውን የሕይወት ውጣ ውረድ ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ እንደ ትምህርት ምቹ ጊዜ ከተመለከትነው "የአሁን ጊዜ ትምህርት" ለማስተማር የሚረዳ ገጠመኝ በሰልጣኙ ሕይወት በተፈጠረ ጊዜ ማስተማር መልካም ነው ምክንያቱም "ለማስተማር የሚመች ገጠመኝ" ሰልጣኙ ያለበትን ሁኔታ የማይመለከት ወቅት ውስጥ ከማስተማር የበለጠ ውጤታማ ስለሆነ፡፡ ለተሳታፊዎች ልታሳስባቸው የሚገባው አንድ ጉዳይ፤ የጎልማሳ ተማሪዎች አንድ ባህርይ የተማረትን ትምህርት ወዲያውኑ በተግባር ማዋል የሚፈልጉ መሆናቸውን ነው፡፡ በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎትም ተመሳሳይ ባህርይ ይንጸባረቃል፡፡ በማማከር እና ድጋፍ ውስጥም የአሁን ጊዜን

እውነታን ያንጸባርቃል እንጂ የረቀ ጊዜን፣ አሁን ካለንበት በተለየ ወደ ፊት የሚገጥምን ሁኔታን አይመረምርም፤ የወደፊቱን የሚያጠናው ስለተስፋ ሲያስብ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም ተስፋ በባህርይው የወደፊት ጊዜ ስለሆነ። እንዲህም ሆኖ የአሁን ጊዜን ለማጥናት እና ለመወያየት የምንከተላቸው ደረጃዎች አሉ። አንድ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት የጠለቀ ዕውቀት ያለው ግለሰብ እንደጻፈው "መልካም የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ለወደፊት የተገባን ተስፋ መልህቅ ሲሆን የሚችል አቅምን ይፈጥራል።"

ተግባር፡- ከተሳታፊዎች መካከል የአሁን ጊዜ ትምህርት ልምድ ያላቸው እና ለተሳታፊዎች ልምዳቸውን ማከፈል የሚፈቅዱ ካሉ ለዚህ የሚናገሩበትን ጊዜ ስጣቸው። ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን አይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ አሳባቸውን መከታተል ትችላለህ፡-

- በዚህ መልክ የተማርከው ትምህርት ከዚህ በፊት ከተማርክበት በምን ይለያል?
- አንደ ጎልማሳ ተማሪነታችን የአሁን ጊዜን መማራችን በበለጠ እንድንማር እና ትምህርቱም ከእኛ ጋር እንዲዋሃድ ወይንም እንዲቀይ ይረዳል?
- ይህን የትምህርት አሰጣጥ ወደ ፊት በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎትህ ላይ ብትተገብር ምን አይነት አስተማሪ የምትሆን ይመስልሃል?

## 3. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋዮች እንደ አዋላጆች ናቸው።

ተግባር፡-

የአዋለጅ ሚና ምን እንደሆነ ተሳታፊዎችን ጠይቅ።

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች "ሌሎች አዳዲስ አሳቦችን፣ አዳዲስ ክህሎቶችን፣ አዳዲስ ምሳሌዎችን እና የመሆን እና የማድረግ መንገዶችን እንዲወልዱ ያግዛሉ። አሰልጣኞች ተማሪዎቻቸው ራሳቸውን አሳብ፣ ራዕይ እና ግብ በሚያምጡበት ወቅት በማዋለድ ይረዷቸዋል።" ተሳታፊዎች በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ አዳዲስ አሳቦች፣ አዲስ ራዕይ ወይንም ግብ ማግኘቱ ለምን እንደሚጠቅመው እንዲያብራሩ ዕድል ስጥ።

## 4. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ በእርሱ ምክር እና ድጋፍ ስር ያሉ ተማሪዎች አማራጮችን እንዲያዩ ይረዳቸዋል።

ሰዎች አንድ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲገቡ አንድ መፍትሄ፣ አንድ ውጤት እና አንድ ተግባር ብቻ በማየት በአንድ ስፍራ "ቆመው ሊቀሩ" ይችላሉ። ታዲያ በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለው አገልጋይ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ሌሎች አማራጮችን እንዲመለከት ይረዳዋል። በዚህም ከግምት ውስጥ ያላስገቡት መፍትሄ ማየት ይጀምራሉ እንዲሁም በጥልቀት እና በልዩነት እንዲያስቡ ምረት

ያገኛሉ። ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች የጋራ ጥረታቸውን በአንድ ጉዳይ ላይ በሚያሳርፉበት ወቅት በፈጠራ የታጀበ አሳብ እና አዲስ የአመለካከት አድማስ ወይንም ነገሮችን የሚከውኑበት አቅም ማግኘት ይችላሉ።

ተግባር፡-

- የተለየ አማራጭ እንድትመለከት ምሪትን ያገኘህበት አጋጣሚካለ እና ማቅረብ የምትችል ከሆነ ከራስህ ልምድ ተነስተህ ምሳሌ ስጥ። ከዚያም ተሳታፊዎች የራሳቸውን ምሳሌ እንዲያቀርቡ እድል ስጥ።
- ተሳታፊዎች በማማከር እና ድጋፍ ስር የሚገኝ ሰልጣኝ የተለየ አማራጭ እንዲመለከት ምሪት የሚያስፈልገው በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ እንዲለዩ በጥያቄ መልክ አቅርብ።
- ተሳታፊዎች በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ የተለየ መፍትሄ እንዲያገኝ የሚያደርጉበት መንገድ ለምሳሌ ሰልጣኙ ቢያንስ ሶስት አማራጮችን ስለገጠመው ችግር እንዲገልጽ ማድረግና እነዚህን አማራጮች እንደ መፍትሄ አሳብ እንዲያቀርብ ጠይቅ። "ይህን ብታደርግ ምን ሊፈጠር ይችላል?" የሚለውን ጥያቄ በመጠየቅ በማማከር እና ድጋፍ የሚያገለግለው ግለሰብ በእርሱ ስር የሚሰለጥነው ሰልጣኝ በእያንዳንዱ የመፍትሄ አሳብ ውስጥ የሚገኘውን መልስ እንዲፈትሽ ያደርጋል።

## 5. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ የሚያነሳሳ ነው።

ሁላችንም የሚያምነብን አንድ ሰው እንፈልጋለን። በተለይ በአገልግሎታችን ያልተሳካልን ሲመስለን እና መደበት ውስጥ ስንገባ፤ ሊያበረታታን የሚችል ባርናባስ ያስፈልገናል።

ተግባር፡-

በመንፈሳዊ ጉዟችሁ ውስጥ በንቃት እንድትጓዙ የሚያነሳሳችሁ ማን ነው? ይህን ግለሰብ በስም መጥራት የሚችሉ ከሆነ፤ ይህ ሰው እንዴት እንዳነቃቃችሁ ለተሳታፊዎች ሁሉ ተናገሩ። ከዚያም ተሳታፊዎችን ሁሉ ሶስት ወይንም አራት አድርጎ በቡድን በመመደብ አንዳቸው ለሌላቸው ስለ "አነቃቂያቸው" እንዲናገሩ አድርግ። አንድ ወይንም ሁለት ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን በመምረጥ ልምዳቸውን ለተሳታፊው ሁሉ እንዲያካፍሉ እድል ስጥ።

## 6. መልካም የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ ጥልቅ አሳቢ ነው።

ነገሮች ነጭ እና ጥቁር ሆነው ስለማይገኙ እንደ አማካሪ እና ደጋፊ በጥልቀትና በዝርዝር ማሰብ እንዲችሉ ሰልጣኞቻችንን ማበረታታት ይኖርብናል። እንደ አማካሪ እና ደጋፊ ሰልጣኞችህ ሳሉበት ሁኔታ መፍትሄ በመስጠት እገጠማቸው ካለው ችግር በላይ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ይገባል።

መልካም የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ለሰልጣኞች የሚከተሉትን ያደርጋል፡-

- ስላለበት ሁኔታ የችግሩን ምንጭ ጨምሮ ወሳኝ የሚባሉ መረጃዎችን ለሁኔታው ይገልጻል፡፡ (ይህም የቤተክርስቲያን ተከላ አደራረግን በተመለከተ ይጨምራል፡፡)
- ችግሩን ለይቶ በጉዳዩ ላይ ብቻ አሳባቸውን ያንጸባርቃሉ፡፡
- የራሳቸውን መላ ምት እንዲለዩ ያግዛል፡፡
- ሌሎችንም ምልከታዎች ከግምት ውስጥ እንዲያስገባ ያግዛል፡፡
- የሚያገለግሉት ህዝብ ያለው ባህል አውድ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

ተግባር፡- ተሳታፊዎች በግላቸው ስለ እነዚህ መገለጫዎች እንዲያስቡ አምስት ደቂቃ መድብ፡፡ ከዚያም ሁለት ወይንም ሶስት በመሆን ከ አስር እስከ አስራ አምስት ደቂቃ በመውሰድ አንዳቸው ለሌላቸው ከእነዚህ ባህርያት ውስጥ የትኞቹ በእነርሱ ሕይወትና አገልግሎት እንደሚንጸባረቁ እና የትኞቹን መገለጫዎች በበለጠ ውጤታማ የሆነ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ክህሎትን ማዳበር እንደሚገባቸው እንዲወያዩ እድል ስጥ፡፡

## ምን እናስወግድ

ይህኛውን ክፍል "ጥሩ ያልሆነ/መርዛማ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ መገለጫዎች" ብለን ልንሰይመው እንችላለን፡፡ ከዚህ በታች የቀረበውን ዝርዝር ተመልከቱ፤ ከመካከላችሁ በጥልቀት ለመወያየት የሚፈልግ ከሌለ ሁሉንም ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ ተወያዩባቸው፡፡ (ማስታወሻ፡- የእነዚህን መገለጫዎች ሙሉ ዝርዝር ማግኘት ከፈለጋችሁ *Masterful Mentoring* በተሰኘው መጽሐፍ ምዕራፍ 7 ላይ ማግኘት ትችላላችሁ፡፡)

- ያለምንም ዋጋ ምክር ይሰጣል፡፡
- ያሄሳል/ሂስ ይሰጣል፤ ሂስ ደግሞ ሲጠየቅ የሚገባውን ትክክለኛ ጥያቄ ያበላሻል፡፡
- በምክርና ድጋፍ ስር ያለውን ተማሪ ሁሌም ከየትኛውም ጉዳት ያስመልጣል፤ ስህተት እንዳንሰራ ከመጠበቅ ይልቅ የበለጠ የምንማረው ከስህተታችን ነው፡፡
- አላስፈላጊ የሆነ የልዩነት አጥር ይገነባል፡፡ በአብዛኛው በእኛ ማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ አልፎን እንዳይሔድ ስለምንፈልግ ሳናስበው የወደፊት እድገቱን የሚያደናቅፍ ግንብ መንገዱ ላይ እንኖራለን፡፡
- "ለምን" የሚለውን ከቁብ አለመቁጠር፤ ለማንኛውም ነገር መሰረት የሆነው አንድ ሌላ ነገር አለ፡ ፡
- በምክርና ድጋፍ ስር ያለን ተማሪውንም ሆነ አሳቡን ዝቅ አድርጎ ይመለከታል፡፡ በእኛ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ስር ያለ ተማሪ የሚያቀርበውን አሳብ ካለመቀበል በላይ የሚያሳንስ ጉዳይ የለም፡፡ ምናልባት በእኛ ስር የሚሰጥነው ግለሰብ እንደተራራ የገዘፈበት ችግር

ለእኛ በጣም ቀላል ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም የሰልጣኞችንን ተራራ እርሱ በሚያይበት ልክ አይተን ካልረዳነው ተገልጋዩን ሊጥለው ይችላል፡፡

ከላይ ያነሳናቸው ስድስቱ ባሕርያት "መርዛማ" የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ በሚለው ርዕስ ስር ተገልጠዋል፡፡ አንዲህ ያሉ አገልጋዮች የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎ የሚፈጠረው ህብረት ብዙ ርቀት ሳይጓዝ በአጭር ይቋጩታል

**ተግባር፡-**

1. ከላይ ለለዘረዘርናቸው ባህርያት ተሳታፊዎች በራሳቸው አገላለጽ እንዲያብራሩ እድል ስጥ፡፡

2. ከቀረቡት ስድስት ባህርያት ውስጥ አደገኛ የሚሉት የትኛውን እንደሆነ እና እስካሁንም አየተንጸባረቀ አንደሆነ፤ ለምን እንዲህ እንደቀጠለ ጠይቅ፡፡ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች ይህን ባህርይ ማስወገድ ወይንም "የተማረትን ማፍረስ" እንደሚችሉ ተሳታፊዎች እንዲወያዩ ጊዜ ስጥ፡፡

## በማማከር እና ድጋፍ ስር ያሉ ሰልጣኞች አስፈልጎት

በዚህ ክፍለትምህርት በማማከር እናድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ ስላሉት ሁለት አስፈልጎቶች ማለትም፡- **የህብረት አስፈልጎት** እና **የመማር አስፈልጎት** ነው፡፡

## የህብረት አስፈልጎት

ሰልጣኞችን ሶስት መሰረታዊ የሆኑ የህብረት አስፈልጎት አቅጣጫዎች አሉት፡- ከእግዚአብሔር ጋር የሚያደርጉት ጉዞ/ህብረት፣ ከቤተሰባቸው ጋር ያላቸው ህብረት እና ከቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ቡድን ውስጥ ያላቸው ህብረት፡፡

በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለ ሰልጣኝ ቅድሚያ ሊሰጥ የሚገባቸው የሕይወት ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፡- አንደኛ መንፈሳዊ ሕይወት፣ ሁለተኛ የቤተሰብ ሕይወት እና ሶስተኛ አገልግሎት ናቸው፡፡ እንዴት ነው ጊዜአችንን፣ ገንዘባችንን እና ሃብታችንን የምናፈስበት ሁኔታ ቅድሚያ ለለምንሰጠው ጉዳይ የሚያሳየው? አንዴትስ ነው ችግሮችን የምንፈታበት እና ውሳኔ የምናስተላልፍበት መንገድ ለየትኛው የሕይወት ክፍል ቅድሚያ እንደምንሰጥ የሚያሳየው?

ተግባር፡- ተሳታፊዎች በማማከር እና ድጋፍ ስር ያለስልጠኛ በየትኛው የሕይወት አቅጣጫ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው አሳባቸውን እንዲሰጡ አበረታታ፡፡ ከዚያም ጠቅላላውን ተሳታፊ ከሁለት በማያንስ ከአራት በማይበልጥ ሰው በማደራጀት ባነሳነው ጉዳይ ዙሪያ አሳብ እንዲለዋወጡ እና ያነሷቸውን አንኳር አሳቦች በጽሑፍ እንዲያሰፍሩ አስር ደቂቃ ያህል ጊዜ ስጣቸው፡፡

ውይይታቸውን ከጨረሱ በኋላ ያስቀመጧቸውን ምላሶች ለጠቅላላው ተሳታፊ እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡ እያንዳንዱ ቡድን የሚሰጠውን መልስ እና አስተያየት በሰሌዳ ወይም በትልቅ ወረቀት ላይ

አስፍር። ተሳታፊዎች የሚያነሱት አሳብ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለ ህብረት ከሆነ እ የሚለውን ፊደል ከፊት አስፍር፣ ቤ የሚለውን ፊደል ደግሞ ለቤተሰብ እና አ የሚለውን ፊደል ለአገልግሎት በማድረግ ከስር ዝርዝር አሳቦችን ጻፉ። ዋናው ነገር እግዚአብሔርን ከፊት ማድረግ ቀዳሚ እንደሆነ፤ ቀጥሎ ደግሞ ቤተሰብን በሶስተኛነት ደግሞ አገልግሎትን ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ትኩረት ሰጥቶ ማቅረብ ነው።

**ተግባራት፡-**

1. እግዚአብሔርን ቀዳሚ፣ ሁለተኛ ደግሞ ቤተሰብ፣ አገልግሎትን ደግሞ ሶስተኛ ማድረግ አስፈላጊነት ምን እንደሆነ ተሳታፊዎችን በመጠየቅ ምላሻቸውን አድምጥ።

2. ተሳታፊዎች በጥሞና ውስጥ በሕይወታቸው ለምን ቅድሚያ እንደሚሰጡ ራሳቸውን እንዲመለከቱ እና እግዚአብሔር የሚላቸውን እንዲሰሙ ጊዜ ስጣቸው። በእርግጥ እግዚአብሔርን ቀዳሚ፣ ቤተሰብን ሁለተኛ፣ አገልግሎትን ደግሞ ሶስተኛ አድርገዋል? ከዚያም እያንዳንዱ ለምን ቅድሚያ እንደሰጠ ምክንያቱን ይናገር። ገንዘባቸውን፣ ጊዜአቸውን እና ሃብታቸውን የሚያፈሱበት መንገድ እንዴት ቅድሚያ ስለሚሰጡት ጉዳይ ይናገራል? እንዴትስ ነው ችግሮችን የሚፈቱበት እና ውሳኔ የሚያስተላልፉበት መንገድ ለየትኛው የሕይወት ክፍል ቅድሚያ እንደሚሰጡ የሚያሳየው?

3. ተሳታፊዎች ሁሉ ሁለት ሁለት ሆነው አንዳቸው ለሌላቸው በሕይወታቸው ለምን ቅድሚያ ይሰጡ እንደነበር ከዚህ ውይይት ያገኙትን እንዲያካፍሉ፤ በዚህም የትኛውን ማስቀጠል እንዳለባቸው፤ የትኛውን ደግሞ ቀደም ተከተል ማስተካከል እንዳለባቸው በተጨማሪነት እንዲወያዩ እድል ስጥ።

**የመማር አስፈልጎት**

በማማከር እና ድጋፍ ስር የሚገኘው ሰልጣኝ ያለው የማማከር አስፈልጎትም ሶስት ነው፡- ዕውቀት፣ መረዳት እና ክህሎት። በሌላ አነጋገር ሰልጣኞችን ተማሪ እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ መሰረታዊ የሆኑ ዕውቀቶች ያስፈልጉታል። ቀጥሎም የተማረትን ትምህርት ዋጋ ያለው መሆኑን መረዳት እና ጊዜ እና ስፍራ በሚፈቅድበት ሁሉ አንዴት እንደሚጠቀሙበት ሊያውቁ ይገባል። በመጨረሻም የአገልግሎት ክህሎታቸውን ማሳደግ ይገባቸዋል። የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች በእነርሱ ስር የሚገኘውን ሰልጣኝ በእነዚህ ሶስት የሕይወት አቅጣጫዎች የሚያደርገውን እድገት ሊያግዙ ይችላሉ።

**ተግባር፡-**

እያንዳንዱ ቡድን በማማከር እና ድጋፍ ስር የሚገኝ ሰልጣኝ ሊኖረው ከሚችለው አስፈልጎቶች ውስጥ ምሳሌ ሊሆን የሚችሉትን ሁለቱን ይጥቀሱ። የሚጠቀሱትን ምሳሌዎች ደግሞ ሰሌዳ ላይ ወይንም ትልቅ ወረቀት ላይ አስፍር። ዕውቀትን በተመለከተ፤ የመማር ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ የሚወሰነው በእነዚህ ሞጁሎች ስልጠና ውስጥ ማለፋቸው ነው።

መረዳን በተመለከተ፤ ለምሳሌ፡- ግልጽ የሆነ ራዕይ መኖር ወይንም ተልዕኮ ተኮር አርፍተነገር የመጻፍ አስፈላጊነት ምንድነው? የሚለውን መመለስ ብቻ ሳይሆን እንዴት ምንያህል ዋጋ ያለው ዕውቀት እንደሆነ እንዲገነዘቡ ያደርጋል፡፡ ከህሉትን በተመለከተ ምንያህል እንደዳበረ የምናውቀው ይህን በመሰለ ጥያቄ ነው፤ ያላቸውን ራዕይ ለሌሎች ግልጥ በሆነ እና ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መልኩ ማስተላለፍ ይችላሉ? "ራዕያቸውን ሌሎች/ቡድኖች ዋጋ እንዲሰጡት" በማድረግ ራዕዩን ይቀሳቀሱ ዘንድ ያስችላሉ?

## ተአማኒነት እና ምስጢር ጠባቂነት

የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት የሚታነጸው በተአማኒነት እና ምስጢር ጠባቂነት መሰረት ላይ ነው፡፡ ከእነዚህ ሁለቱ ግብአቶች አንዱ የጎደለ እንደሆን አገልግሎቱ ወደ ከአንገት በላይ ይሆናል ከዚህ ከከፋ ደግሞ ህብረቱ ይፈርሳል፡፡

ተግባር፡- ተሳታፊዎች ተአማኒነት እና ምስጢር ጠባቂነት ለእነርሱ ምን እንደሆኑ እንዲያብራሩ ጠይቅ፡፡ ከዚያም እነዚህ ሁለት ግብአቶች በማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ውስጥ ለሚፈጠር ጤናማ ህብረት ለምን ወሳኝ እንደሆኑ ጨምረው እንዲያብራሩ ጠይቅ፡፡

### ህብረትን የተመለከቱ የአድርግ አታድርግ መመሪያዎች

### 1. አክብር፤ አሳንሰህ አትመልከት

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች በእነርሱ ስር ያሉትን ሰልጣኞች ማክበር አለባቸው ምክንያቱም ተማሪዎቹ ያለምንም ፍርሃት እና ሃፍረት ራሳቸውን በግልጥ ለማቅረብ እና ሃቀኛ ይሆኑ ዘንድ ፈቃድ የሚያገኙት ዝቅ አድርገን ከተመለከትናቸው ብቻ ስለሆነ፤ ይህም ብቻ ሳይሆን ለተማሪዎቻቸው ስሜት፣ ልምድ እና ጥረት ትኩረት መስጠት እና መልካም የሆነውን ማበረታታት እንድሁም ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ጨዋ በሆነ እና አክብሮት በተሞላ መንገድ ማረም አስፈላጊ ነው፡፡

### 2. ዋጋ ስጥ፤ ዋጋ ቢስ አታድርግ

እያንዳንዱ ሰው ለማንነቱ ዋጋ እንዲሰጠው ይፈልጋል፡፡ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች መሪነታቸው በተማሪያቸው ላይ ጌታ እንዲሆን መፍቀድ የለባቸውም፤ ዝም ብለውም ሰልጣኙ ሲያሻሽለው በሚገባ የሕይወት ዘርፍ ላይ ብቻ እጃችንን እየጠቆሙም አይሆንም፡፡ ከዚህ ይልቅ በማማከር እና ድጋፍ የሚያገለግሉትን ሰልጣኝ እንደ አንድ ሰው መቀበል ይጠበቅባቸዋል፡፡

ተግባር፡- ተሳታፊዎች ገላ 5፡13፤ ኤፌ 5፡ 21 እና ሮሜ 12፡10ን በማንበብ እንዚህ ክፍሎች ካነሳነው ነጥብ ጋር እንዴት እደሚገናኙ ለማወቅ ይወያዩ፡፡

### 3. ሞዴል ሁን፤ ጣልቃ አትግባ፡፡

ኢየሱስ አገልግሎትን እና ባህርይን ለደቀመዛሙርቱ ሞዴል በመሆን አሳይቷል፡፡ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮችም ተመሳሳዩን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ አንድ

ሲያስወግዱት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር ሰልጣኞቸው ባልጋበዛቸው ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባትን ነው።

### 4. አረጋግጥ፤ አትኮንን።

ሰልጣኙህ አንድን ጉዳይ በትክክል እንደከወነ አረጋግጥ ከዚያም ውሳኔያቸውን አክብር።

### 5. አበረታታ፤ ተስፋ አታስቆርጥ።

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ረዳት ሲሆን እንደሚችል ሁሉ በተቃራኒው ደግሞ ተስፋ አስቆራጭ ሊሆን እንደሚችል ተሳታፊዎችን አሳስብ።

**ተግባር፡-**

ከተሳታፊዎች ጋር 1ተሰ 5፡11ን አንብቡና፤ ተሳታፊዎች ከዚህ ጋር ይስማማል ብለው የሚያስቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንዳለ እንዲያቀርቡ እድል ስጥ።

### 6. አነሳሳ፤ ወኔን አታጥፋ።

የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ ለሰልጣኞቻቸው በአብዛኛው ማለት ያለባቸው "ልታደርገው ትችላለህ" እንጂ "አይ...አሁን በእጅህ ያለው ጉዳይ በጣም ከባድ ይመስለኛል" የሚል መሆን የለበትም።

**ተግባር፡-**

ሁልጊዜ አይሆንም የሚል እና ማንኛውንም ነገር ለመስራት ሲነሱ እንደማይሳካላቸው የሚነግራቸው ግለሰብ ያውቁ እንደሆን ተሳታፊዎችን ጠይቅ። ይህ ምን አይነት ስሜት ይፈጥራል? እንዲህ ያለው "ምክር" ጠንከረው እንዲሞክሩ የሚረዳ ነው ወይስ ተስፋ የሚያስቆርጥ? አንድን ሰው ያለማቋረጥ አሳቡ እንደማይሳካ ስንነግረው ምን ሊሆን ይችላል?

### 7. ጸልይ፤ ሌሎች ምንም እንደማያውቁ አድርገህ አታስብ።

ጳውሎስ በፊሊጲስዩስ ለሚገኙ አማኞች እንዲህ ብሏል "ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር" ፊሊ 2፡3። ሌሎች ምንም እንደማያውቁ ማሰብ፤ በሰዎች ላይ እንደ ሊቅ ራሳችንን በመኮፈስ እንድንቀርብ ያደርገናል። በዚህም ከሌሎች በላይ ራሳችንን የተሻለ ለሰው አድርጎ የማሰብ ዝንባሌን ያመጣብናል።

**ተግባር፡-**

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች ጸሎት የሚያገለግሉትን ተማሪ ዝቅ አድርገው እንደይመለከቱ እንዴት እንደሚረዳ ተሳታፊዎች እንዲናገሩ እድል ስጥ።

## ክህሎትን የተመለከተ የአድርግ አታድርግ መመሪያ

### 1. አድምጥ፤ አታውራ።

አስታውስ ሰው አንድ አፍ እና ሁለት ጆሮ ኖሮት ነው የተፈጠረው። ይህ ስለ ማማከር እናድጋፍ አገልግሎት ስለሚመሰረት ህብረት ምን ያስተምረናል?

**ተግባር፡-**

ሙሉ ክፍለጊዜውን ራሱ ብቻ ከሚያወራ አስተማሪ ምን ያህል ትምህርት እንደሚያገኙ ተሳታፊዎችን ጠይቅ እና አሳባቸውን ስማ፡፡ እንዲህ ያለው ትምህርት ለራሳቸው እንዲያስቡ እድል ይሰጣል ወይንስ አስተማሪው የተናገረውን ብቻ መላልሰው እንዲያስቡ ያደርጋል? ይህን ትምህርት እንለዋለን ወይንስ እንዲያው ውጤት የሌለው ጉንጭ አልፋ ወሬ ነው?

## 2. ጠይቅ፤ አንትናገር፡፡

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ዝም ብሎ የሚያወራ ከሆነ የሰልጣኙን ፍላጎት እንዴት በመንፈስ ሊመረምር ይችላል? አገልጋዩ ብዙ ጥያቄ እየጠየቀ ተማሪውን መስማት እንጂ መልስ ለመስጠት ተዘጋጅቶ ህብረቱን መጀመር ተገቢ አይደለም፡፡ ራስን ማግኘት የሚፈጠረው አገልጋዩ ለተማሪው ምን ማሰብ እና ማድረግ እንዳለበት ከመንገር ይልቅ ተማሪውን በመጠየቅ እና በማድመጥ ነው፡፡

## 3. አጥርተህ አቅርብ፤ እንዲህ ይሆናል ብለህ አትገምት፡፡

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች ሰልጣኞቻቸው ምን አንደ ሚፈልጉ እና ምን እየጠየቁ እንዳሉ መረዳታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን አገልጋዩ ለተማሪው ያለበትን ሁኔታ የማይመለከት ራሱ ያዘጋጀውን ምላሽ ሊሰጠው እንዲሁም ተገልጋዩ ያማያስፈልገውን መረዳት ሊጭንበት ይችላል፡፡

## 4. አሳብህን በሚገባ ግለጥ፤ ዝም ብለህ አታፍስስ፡፡

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች ለተማሪዎቻቸው የሚያስፈልጋቸው እና የሚረዳቸው መረጃ ምን እንደሆነ በሚገባ መግለጥ ይገባቸዋል፡፡ ዝም ብለው መረጃውን በሰልጣኞቸው ላይ ማፍሰስ አስፈላጊ አይደለም፡፡

**ተግባራት፡-**

- መረጃን ያለ ምንም ምክንያት በሌሎች ሰዎች ጭንቅት ውስጥ ማፍሰስ ለምን ብዙ ሰዎች ቀላል እንደሆነ ተሳታፊዎችን ጠይቅ፡፡ የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች ሰልጣኞቸው በአጠረ ጊዜ ሁሉን አውቆ እንዲጨርሱ አቋራጭ መንገድ ይፈልጋሉ?
- ከተሳታፊዎች መካከል ወደ ኮምፒዩተር ባለሙያ ሄዶ የሚያውቅ ሰው እንዳለ ጠይቅ፡፡ ታዲያ ምናልባት ጥያቄአችሁ እንዴት አድርጎ ወረቀት ላይ ለማተም ከማተሚያ(ፕሪንተር) ጋር እንዴት ማገናኘት እንዳለባችሁ እንዲያሳያችሁ ሆኖ፤ እርሱ ግን ከእናት ኮምፒዩተሩን ወስዶ እራሱ ወረቀት ላይ ማተም የምትፈልጉትን አትሞ ለእናንተ ምንም ሳያሳያችሁ መልሶላችሁ ያውቃል? ወይንም ሞባይላችሁ ላይ እናንተ የማታውቁት አንድ መጠቀሚያ (አፕሊኬሽን)

ገጥሟችሁ እንዴት እንደሚስተካከል ይነግረኛል ብላችሁ ለሚያውቅ ሰው ስትሰጡት፤ ለእናንተ ሳያሳይ ራሱ አስተካክሎ ሰጥቷችሁ ያውቃል፤ ወይንም እንደዚህ አይነት ሌላ ጉዳይ ገጥሟችኋል? እንዲህ ባለው ወቅት ተማሪ ማወቅ የሚገባውን እንዲያውቅ ምን ማድረግ ይገባናል? ኮምፒዩተር የሚያውቀውም ሆነ ሞባይል ዕውቀት ያለው ምን ማድረግ ነበር የሚጠበቅባቸው? የኮምፒዩተር ወይንም ሞባይል እንዴት እንደሚስተካከል የሚያውቀው ሰው እንዲያ ከማድረግ ይልቅ ምን ማድረግ ነበረበት? እንዴት ነው ይህ ጽንሰ ሀሳብ፤ ሀሳብህን በሚገባ ግልጥ ለሚሰው እንደምሳሌ ሊያገለግል የሚችለው?

## 5. አጀንዳ ይኑርህ፤ የማማከር እና ድጋፍ ክፍለትምህርትን ያለ ምንም መርሃ ግብር አትጀምር፡፡

አጀንዳ ሰዎች በተጠሩበት ጉዳይ ላይ ብቻ አትኩረው እንዲሰሩ እድል ይሰጣል፡፡ አጀንዳ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

- በማማከር እና ድጋፍ የምናገለግለው ተማሪ የእግዚአብሔር መገኘት በስብሰባቸው እንዲሆን እንዲጸልይ መጠየቅ፡፡ ጸሎት መጀመሪያ ወይም መጨረሻ ላይ ብቻ ሳይሆን በስብሰባው መሃልም እንደየአስፈላጊነቱ መጸለይ ትክክል ይሆናል፡፡ መቼም ቢሆን ጸሎት በዛ አይባልም!
- ምንም እንኳን በአጀንዳችን ያስቀመጥነውን ሀሳብ አንዳንጨርስ የሚያደርገን እንኳን ቢሆን፤ ሰልጣኞችን ሊጸለይለት የሚገባ የሚያሳስበው ነገር ካለ መጸለይ ግድ ነው፡፡
- ከቀደመው ስብሰባችሁ የቀጠለ ሀሳብ ካለ በእርሱ ለመጀመር አጀንዳ መያዝ፡፡ ከዚህ ቀደም የተማራችሁትን እንደገና በመከለስ እና ሀሳባችሁን በማንጸባረቅ ይህኛውን ትምህርት ጀምሩ፡፡ በመቀጠልም የሰልጣኙን እመርታ/ለውጥ በባለፈው ትምህርት ማብቂያ ላይ የተካተቱትን የተግበራ ነጥቦችን በማንሳት መዝኑ፡፡
- ልታቀርብ የምትፈልገውን አዲስ ሀሳብ አካፍል፡፡
- ይህኛውን ክፍለትምህርት እንዳበቃችሁ ሰልጣኙ ራሱ የትግበራ ነጥቦችን እንዲለይ አድርግ፡፡
- በትምህርቱ ውስጥ ስለመጣው መልእክት እና ከዚያም በኋላ እንዲለየው ባቀረብክለት የትግበራ ነጥቦች እና እንዚህን ተከትሎ ሊሰራ ያለውን ስራ መሰረት ያደረገ ጸሎት ለተሳታፊው ጸልይ፡፡

አጀንዳ ይዞ መንቀሳቀስ የማማከር እና ድጋፍ አገልግሎት ሂደቱ ያለምንም እንቅፋት እንዲጓዝ እድል ይፈጥራል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የማማከር እና ድጋፍ

አገልጋዩ ሳስቀመጠው አጀንዳ ባርያ መሆን የለበትም፤ በተለይ ሰልጣኙ ይዞት የሚመጣው አጣዳፊ እና ያልተጠበቀ ፍላጎት ካለ ከምንም ቀድሞ ያን ማስተናገድ ተገቢ ስለሆነ።

## 6. ጊዜ ስጥ፤ አቋራጭ አትጠቀም።

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ከሰልጣኙ ጋር ሲፈጥረው የሚገባውን ህብረት ለመፍጠር በቂ ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አለበት። አቋራጭ ለመጠቀም መሞከር የለበትም። ተአማኒነት እና ምስጢር ጠባቂነትን በህብረት ውስጥ ለማምጣት ጊዜ ይወስዳል፤ በአንድ ጀምበር የሚመጣ አይደለም።

## 7. ምራ፤ ነገሮችን ለማስተግበር ሌሎችን አታስጨንቅ/አትንዳ።

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋይ ሰልጣኙን ይመራል እንጂ "ዱላ" ይዞ "እንደ ከብት" አይነዳውም። ከዚህ ይልቅ "አዳዲስ አሳቦችን፣ አዳዲስ ክሎቶችን፣ አዳዲስ ገላጭ ምሳሌዎችን እና የመሆንና የመስራት አዳዲስ መንገዶችን ጸንሶ እንዲወልድ ያግዛል።"

## 8. ደግመህ ተመልከት፤ የበሰለ ለውጥ እንዲመጣ ከመግፋት አትቦዝን።

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ እና ሰልጣኙ በሚገናኙበት ስብሰባ ሁሉ ከዚህ ቀደም ስለተወያዩበት እና በሰልጣኙ ላይ ስለመጣው ለውጥ መገምገም ይኖርባቸዋል። የበሰለ ለውጥ እንዲመጣ መገፋፋት ሰልጣኙ አዳዲስ ጽንሰ አሳቦችን እንዲያስታውስ፣ የተማራቸውን አዳዲስ መረጃዎች በተግባር እንዲያውል እና የአገልግሎት ሂደትን እንዲያዳብር ዘንድ ያስታውሰዋል።

## 9. ግብአት ሁን፤ አትመራመር።

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዩ ራሱን ለተገልጋዩ ጠቃሚ እንደሆነ ግብአት ማቅረብ ይጠበቅበታል፤ ከዚህም በተጨማሪ ወደሌሎች ግብአቶችም ማመላከቱን እርግጠኛ መሆን ይኖርበታል። የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች ምርምሩን ራሳቸው ማድረግ የለባቸውም፤ ምክንያቱም የሚመሯቸው ሰልጣኞች ጎልማሳ እንደመሆናቸው ራቸውን መምራት ይገባቸዋል ደግሞም ይችላሉ።

**ተግባር፡-**

በማማከር እና ድጋፍ ስር ላለ ሰልጣኝ ይበጃል የሚሏቸውን ግብአቶች ተሳታፊዎች እንዲዘረዝሩ አድርግ። ግብአቶቹም የሚከተሉትን ማካተት ይኖርባቸዋል ሌሎች ሰዎች፣ መጽሐፍት፣ መዛግብት፣ ፊልሞች፣ የድምጽ መልዕክቶች፣ ድረገጾች እና ብሎጎችን።

## 10. የእይታ ምርጫን አቅርብ፤ ሁልጊዜ ያለቀለት መልስ አትስጥ።

የማማከር እና ድጋፍ አገልጋዮች ሰልጣኞቻቸው አማራጮችን፣ የተከፈቱ የስራ በሮችን እና አዳዲስ ዕድሎችን እንዲመለከቱ ማገዝ ያስፈልጋል። ይህ ማለት፤ ቀድም እንደነሳነው ያለቀለት መልስ ማዘጋጀት አለባቸው ማለት አይደለም።